**ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ**

**የማህበረሰብ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ የቴኣትር ጥበባት ትምህርት ክፍል**

# "አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪ አሳሳል አንፃር ትንተና"

**በ**

**በለጠ ጥላሁን**

**በማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ ለቴኣትር ጥበባት ትምህርት ክፍል**

**ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ**

**ጉብሬ፣ ወልቂጤ፣ ኢትዮጵያ**

**ግንቦት 2017**

''አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንጻር ትንተና''

በ

በለጠ ጥላሁን

አማካሪ

መምህርት ቤቴልሔም አንጃ

በማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብዕ ኮሌጅ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጉብሬ፣ ወልቂጤ፣ ኢትዮጵያ

ግንቦት 2017

# ማረጋገጫ

ይህ በተማሪ በለጠ ጥላሁን "አልተዘዋወረችም" ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንጻር የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የዩኒቨርሲቲዉን ደረጃ ያሟላ እና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነዉ፡፡

የአማካሪዉ/ዋ ስም ቤተልሄም አንጃ
ፊርማ..................................

ፈታኝ1.............................................. ፊርማ...........................

ፈታኝ2.............................................. ፊርማ............................

# አበርክቶ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መታሰቢያነቱ በወጣትነቷ ለሞተችው ለአክስቴ ስመኝ አንላይ ይሁንልኝ።

## ምስጋና

በመጀመሪያ ምህረትህ ይቅር ባይነትህ ወደር የሌለዉ አልፋ እና ኦሜጋ የድግል ማርያም ልጅ ከእናትህ ጋር ተመስገንልኝ። በመቀጠል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ እዚህ ላደረሳችሁኝ ቤተሰቦቼ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ። ሳትሰለች በትህትና እና በትግስት ስህተቶቼን እያረመች ይህን ስራ እንድጨርስ ለረዳችኝ መምህርት ቤተልሄም አንጃ ከልብ አመሰናለሁ። ሁለም ከጎኔ ለነበራቹ ጋደኞቼ እወዳቹሃለሁ አመግናለሁ። በአጠቃላይ ከጎኔ ለነበራቹ መምህራኖቼ ምስጋናየ ይድረሳቹ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ መሰረት ያደረገው አልተዘዋወረችም በተሰኘ ልቦለድ ከገፀ ባህሪያ አሳሳል አንፃር ትንተና ማድረግ ነዉ። አጥኝው በምዕራፍ አንድ መግቢያ ላይ የኪነ ጥበብ ምንነት፣ የሰነ ፅሁፍ ምንነት፣ የልቦለድ እና የገፀ ባህሪያት ምንነትን ገልጿል። በተጨማሪም የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና ለጥናቱ የተጠቀማቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን አብራርቷል። በምዕራፍ ሁለት ገፀ ባህሪያት በእውኑ አለም የሌሉ የደራሲው ፈጠራ ሰዎች መሆናቸውንና የገፀ ባህሪያት አሳሳል ምንነት በደንብ ገልፆታል። በምዕራፍ ሶስት የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክና ልቦለዱ አራት ገፀ ባህሪዎችን ወክሎ በእነሱ የህይወት ጉዞዎች መካከል ተወስዶ በጥናት ላይ የተመሰረተ ልቦለድ መሆኑን አብራርቷል። በተጨማሪም የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ዋና ገፀ ባህሪያቶች በልቦለዱ ዉስጥ ያላቸውን ሚና አብራርቷል። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦችን ያስቀመጠ ሲሆን ለዚህም አይነተኛ(Qualitative research) የምርምር ዘዴ ተጠቅሟል።

## ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

ማረጋገጫ

አበርክቶ

ምስጋና

አጠቃሎ

**ምዕራፍ አንድ**......1

1 መግቢያ......1

1.1 የጥናቱ ዳራ......2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት......3

1.3 የጥናቱ አላማ......4

1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ......4

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ......4

1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች......4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ......4

1.6 የጥናቱ ወሰን......5

1.7 የጥናቱ ዘዴ......5

1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች......6

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት......6

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች......6

1.9.1 ለችግሩ የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሳቦች......6

**ምዕራፍ ሁለት**......7

2. ክለሳ ድርሳናት.......................................................................................7

2.1 የገፀ ባህሪያት ምንነት.......................................................................................7

2.2 የገፀ ባህሪያት አሳሳል ምንነት ...........................................................................8

2.2.1 አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል.......................................................................10

2.2.2 ማህበራዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል....................................................................11

2.2.3 ስነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል...................................................................11

2.2.4 ሞራላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል......................................................................12

2.3 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት.......................................................................................13

**ምዕራፍ ሶስት**.......................................................................................14

3.1 የመረጃ ትንተና.......................................................................................14

3.1.1 የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ........................................................14

3.1.2 የገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና.......................................................................15

3.1.3 ደካማ ጎን.......................................................................................26

3.1.4 ጠንካራ ጎን.......................................................................................26

**ምዕራፍ አራት**.......................................................................................28

4.1 ማጠቃለያ.......................................................................................28

4.2 መፍትሄ ሀሳቦች.......................................................................................28

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ኪነ ጥበብ የሰው ልጅ የእለት ተዕለት ኑሯቸውን በፈጠራቸው አካተው የሚያሳዩበት እና ስሜታቸውን ወይም ሀሳባቸውን የሚገልፁበት የጥበብ ዘዴ ነው። ኪነ ጥበብ በውስጡ ብዙ የጥበብ ስራዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን ስነ ፅሁፍም ከኪነ ጥበብ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። ስነ ፅሁፍ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ሰዎች የእለት ተዕለት ኑሯቸውን እና ስሜታቸውን የሚገልፁበት ሰዎች ከአይምሯቸው የሚያመነጩት ፈጠራዊ ሀሳብ ነው።። ሰለ ስነ-ፁሁፍ በዘሪሁን አሰፋው የስነ-ፁሁፍ መሰረታዊያን ላይ እንዲህ ተገልጿል።

> የሰው ልጅ የሀሳብ መግለጫ ከኪነ-ጥበብ ዘርፎች አንዱ ሰነ-ፁሁፍ ነው።
>
> ሰነ ፁሁፍ በቁሙ ሲታይ ስነ-ፁሁፍ የሚለው ቃል በፁሁፍ የተቀመጠውን
>
> ወይም የተቀለፀውን ብቻ የሚያመለከት መሆኑ ግልፅ ነዉ። የሰው ልጅ
>
> የፅህፈት ባህል ለመጀመሩ አስቀሞ ሰሜቱን የሚገልፅባቸው ቃላዊ ፈጠራዎች
>
> እንደነበሩ ይታወቃል፣ አሁንም ቢሆን አሉ ወደፊትም ይኖራሉ። ስነ-ፅሁፍ
>
> ስንል ህልውናቸው በቃል የሆነዉን ፈጠራዊ ሃሳብ መገለጫ ቅርፃችንም
>
> ጮምር መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። /ዘሪሁን አስፋው: 2007 : 11/

ከዚህ እንደምንረዳው ስነ ፅሁፍ ከኪነ ጥበብ ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑን እና ሰዎች ሰዎች የእለት ተዕለት ገጠመኞቻቸውን እና ስሜታቸውን ፅሁፋዊ በሆነ መንገድ የሚያንፀባርቁበት የጥበብ ስራ ነው። ስነ ፅሁፍ ቃላዊውን ወዴ ፅሁፍ የምናመጣበት እና የሰዎችንም የፈጠራ ክህሎት ወይም ችሎታን የሚጠይቅ የጥበብ ዘርፍ ነው።

ስነ ፅሁፍ በዉስጡ ልዩ ልዩ መስኮችን የያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥም አንዱ ልቦለድ ነው። ልቦለድ ካሉት ከስነ ፅሁፍ ዘርፎች አንዱ ነው። ልቦለድ ደራሲው በምናቡ ውስጥ የሳላቸውን ገፀ ባህያት በእውኑ አለም ውስጥ የሌሉትን በእራሱ ፍልስፍና በእውኑ አለም ውስጥ ያሉ አስመስሎ የህይወት ውጣ ውረዶችን(ገጠመኞችን) ወይም ደግሞ ድርጊቶችን በጽሁፍ መልክ አድርጎ ለተደራሲያን የሚያቀርብበት የጥበብ አይነት ወይም ዘዴ ነው። ልቦለድ ማለት በእውኑ አለም ውስጥ የሌለ የደራሲው የፈጠራ ስራ ነው። ገፀ ባህሪ ከልቦለድ አላባውያን ውስጥ አንዱ ነው።

ገፀባህሪ ከልቦለድ አላባውያን ውስጥ የሚካተት ሲሆን ገፀባህሪያት በገሀዱ አለም ፍጡራን አካልና አምሳል ተለክተው የሚቀረፁ የደራሲው የፈጠራ ሰዎች ናቸው። እነዚህ የደራሲው የፈጠራ ሰዎች ልክ እንደ እውኑ አለም ሰዎች ነው የሚሳሉት ይራባሉ፣ ይጠማሉ፣ ይጣላሉ፣ ይፋቀራሉ። ገፀባህሪያት የሚከውኑት ድርጊቶች በሙሉ በደራሲው አማካኝነት የተሰጣቸውን ነገር በመሆኑ እንደራሳቸው ሳይሆን እንደደራሲው ፍላጎት በመሆን ደራሲው ወደሚመራቸው አቅጣጫ ይጓዛሉ። ይስማክ ወርቁ "የኦጋዴን ድመቶች" በሚለው ልቦለድ መፅሀፉ መግቢያ ላይ ስለ ገፀ ባህሪያት እንዲህ ሲል ገልፆታል፡-

> ገፀ ባህሪያት በአንድ የፈጠራ ፅሁፍ ዉስጥ የታሪኩ ባለቤት ሆነው
> 
> የሚቀርቡ ናቸው። እነዚህ የታሪክ ባለቤት የሆኑ ገፀ ባህሪያት በደራሲው
> 
> ምናብ የሚፈጠሩ እና ከገሀዱ አለም ሰዎች ጋር በአካል እና በምግባር
> 
> የሚመሳሰሉ ሰዎች አልያም ሌሎች ፍጡራን ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ
> 
> የምናብ አለም ፍጡራን የሰውን አጠቃላይ ባህሪን የሚወክሉ ናቸው።
> 
> /ይስማክ ወርቁ: 2012፤ 1/

ገፀ-ባህሪ ታሪክን ይዘዉልን የሚጓዙ በእውነቱ አለም ሊኖሩም ላይኖሩም የሚችሉ በሰው፣ በእንስሳ፣ በቁሳቁስ እና የመሳሰሉት የደራሲው ፈጠራ ታክሎበት ሊወክሉ የሚችሉ ናቸው። ገፀ-ባህሪ ሰዋዊ ባህሪ ሊታዩባቸዉ ይችላሉ፤ የራሳቸው መለያ ባህሪ ይኖራቸዋል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስነ–ፅሁፍ የሰው ልጆች ክህሎት አቅም የፈጠራ እና የሙያ ዘርፍ ነው። ስነ ፅሁፍ ሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮአቸውን ከፈጠራ ጋር አካተው የሚያሳዩበት በዉስጡ ብዙ ልዩ ልዩ መስኮችን የያዘ ነው።። ስነ ፅሁፍ (Literature) በቋንቋ የተጻፉ ወይም የተቀረጹ የፅሁፍ ስራዎችን የሚገልጽ ጥሬ የሆነ ዋና ዋና ጽሑፎችን፣ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ድራማዎችን፣ ወዘተ ያካትታል። እንደ ሥነ ጥበብ ዓይነት፣ ስነ ፅሁፍ የሰው ልጅን ስሜት፣ ህልም፣ ልምድ፣ ታሪክ፣ እና ማንነት በገጽታ የሚገልጽ መሣሪያ ነው።

ስነ ፅሁፍ ዋና አላማው ማንነትን እና ባህልን ለማስተላለፍ፣ የሰው ልጅን ስሜት እና አስተሳሰብ ለማንፀባረቅ በተጨማሪም ማህበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለመናገር የምንጠቀምበት ጥበባዊ ዘዴ ነው። ስነ ፅሁፍ ችሎታን የሚጠይቅ የሰው ልጅን ህይወት እና ልምድ በቃል ወይም በፅሁፍ የሚያንፀባርቅ ጥልቀት ያለው አካል ነው።

ልቦለድ የጽሑፍ ዓይነት ሲሆን ይህም የሰው ልጆችን ህይወት፣ ስሜቶች፣ እና አስተሳሰቦች የሚያሳይ ረጅም ወይም አጭር ታሪክ ነው። ልቦለድ በተለይ የሚጻፈው በ ዝ ር ው መልኩ ሲሆን ከግጥም የተለየ ነው። የልቦለድ ስራዎች ብዙውን ጊዜ የሚያተኩሩት በግለሰቦች የአኗኗር ዘይቤ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ነው፣ እና አንባቢውን በስሜትም ሆነ በአስተሳሰብ ለመሳብ ይሞክራሉ። ልቦለድ የሰው ልጆችን ህይወት እና ስሜቶች የሚያሳይ የፈጠራ ጽሑፍ ነው። ልቦለድ መሰረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ጉዳዮችን ማለትም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሴቶችን መሰረት አድርጎ ለአንባቢ አንዳች ትምህርት ሊሰጥ በሚችል መንገድ የሆነውን፣ የተደረገውን ወይም ቢደረግ የሚለውን ምኞቱን ወይም ፍላጎቱን ስነ ፅሁፋዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብበት የኪነ–ጥበብ ዘርፍ ነው። ልቦለድ በገፀ–ባህሪያት ተወክሎ፣ መቼት፣ ሴራ እና ጭብጥ ተሰቶበት የማህበረሰቡን እንቅስቃሴን እና የህይወት ሑደትን ተከትሎ በአንድ በተመረጠ ታሪክ ላይ ፣ በተመረጠ ጊዜ እና ቦታ ተወስኖ የሚጻፍ የሰነ–ፅሁፍ አይነት ነው።

ገፀ ባህሪ ማለት በልቦለድ አለም ውስጥ ስጋ ለብሰው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው፣ ተጠምተው፣ ተርበው፣ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ፣ የሚጣሉ እና የሚፋቀሩ ወይም የሚዋደዱ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው። ገፀ-ባህሪም ውጫዊና ውስጣዊ ስብዕና የተሸከመ ሲሆን ሰው፣ እንስሳ፣ ግውዝ ነገር ወዘተ ሊሆን ይችላል በአጠቃላይ ታሪኩ በእነማን ይነገራል? እነማን አሉበት? በሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጠን በገፀ-ባህሪው ነው። ስለ ገፀ ባህሪያት ደበበ ሰይፉ "ከፀሐፊ ተውኔት አንፃር" በሚለው መፅሀፊ እንዲህ ሲል ይገልፃል "በገሀዱ አለም ውስጥ አፋዊና ህሊናዊ መልክ ያላቸው ሰዎች ይመሳሰላሉ።" /ደበበ ሰይፉ፣1973፣23/

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያጠቃልለው "አልተዘዋወረችም" ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ማለትም ከአካላዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል፣ ከስነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል፣ ከማህበራዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል እና ከሞራላዊ የ ገ ፀ ባ ህ ሪ አሳሳል አንፃር በልቦለዱ ውስጥ ምን እንደሚመስሉ መዳሰስ ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

❖ አጥኝው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት እእንዲያካሄድ መነሻ የሆነው ምክንያት በዋናነት፡-

- አጥኝው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ካነሳሱት ምክንያቶች በዋናነት ከዚህ በፊት በ"አልተዘዋወረችም" ልብ ወለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች ባለመኖራቸው አጥኝው ይሄን ጥናት ለመስራት ካነሳሱት ምክንያቶች አንዱ ነው።
- በተጨማሪም "አልተዘዋወረችም" ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር በመተንተን ያለውን ደካማ እና ጠንካራ ጎን ለማወቅ እና ለተደራሲያን ለማሳወቅ ስለፈለገ ነው።

### 1.3 የጥናቱ አላማ

#### 1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ

- የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አብይ አላማ "አልተዘዋወረችም" ረጅም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ትንተና ማድረግ ነው።

#### 1.3.2 የጥና ንዑስ አላማ

- የዚህ ጥናታዊ ፅሐፍ ንዑስ አላማ ስለ ገፀ ባህሪያት ምንነት መሳወቅና ትምርታዊ ውጤት ማስገኘት
- አራቱ የገፀ ባህሪ አሳሳል ዘዴዎችን በመግለፅ በአልተዘዋወረችም ልቦለድ አራቱ የገፀ ባህሪ አሳሳል ዘዴዎችን በገፀ ባህሪያቶች ላይ እንዴት እንደተጠቀማቸው ማሳወቅ ነው

### 1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከአራቱም የገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ምን አይነት ክፍተት አለው?
- አልተዘዋወረችም ልቦለድ አራቱን የገፀ ባህሪያት የአሳሳል ዘዴዎችን እንዴት ተጠቅሟል?
- አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አኳያ ማለትም ከአካላዊ፣ ከሞራላዊ፣ ከስነ ልቦናዊ እና ከማህበራዊ ያለው ደካማና ጠንካራ ጎን ምንድን ነው?

### 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት "አልተዘዋወረችም" ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንጻር በመተንተኑ የሚከተሉትን ጠቀመታዎች ይሰጣል፡-

- የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋነኛ ጠቀሜታ "አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር በመተንተን በገፀ ባህሪያት አሳሳል ላይ የነበራቸውን ድክመት እና ጥንካሬ ያሳውቃል።
- አልተዘዋወረችም ልቦለድ አራቱ የገፀ ባህሪ አሳሳል ዘዴዎችን እንዴት እንደተጠቀማቸው እና ምን አይነት ክፍተቱን በማውጣት ግንዛቤ ይሰጣል።
- በተጨማሪም ወደፊት ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር እና ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት

ያላቸዉ ጥናታዊ ጽሁፍ ለሚሰሩ አጥኚዎች እንደ መረጃ ምንጭ ያገለግላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን አልተዘዋወረችም ረጅም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ማለትም ከአካላዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል፣ ከማህበራዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል፣ ከስነ ልቦናዊ የ ገ ፀ ባ ህ ሪ አ ሳ ሳ ል እና ከሞራላዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል አንጻር መተንተን ላይ ብቻ ይወሰናል።

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማጥናት አጥኚው አይነታዊ(Qualitative) የምርምር ዘዴ በመጠቀም ጥናቱን የሚያካሂድ ይሆናል። አይነታዊ የምርምር ዘዴ ማለት ቁጥራዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት እና በመተንተን

ለችግሮች መፍትሄ የማግኛ ዘዴ ነው። ስለ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ያለው እንዳወቀ "የምርምር መሰረታውያን መርሆች እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ገልፆታል።

> *አጥኚው ምርምሩን የሚያካሄደዉ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ነዉ ከሚሰበሰቡ የመረጃ አይነቶችና የአተናተን ዘዴዎች አንፃር ምርምርን በሌላ መልኩ ደግሞ ተመራማሪው የሚሰበስባቸዉን የመረጃ አይነቶች እና የተሰበሰቡትን ለመተንተን የሚከተላቸው ዘዴዎች አንፃር ምርምር በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። መጠናዊ ምርምር እና አይነታዊ ምርምር ናቸው።* በምርምር ሂደት ሁሉም ነገሮች የሚገለጡ ወይም የሚወከሉ አይደሉም። አጥኝው ለማጥናት የፈለገዉን ርዕሰ ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በአይነት የሚገለጽ ይሆናል። ስለዚህ በአይነታዊ ምርምር አጥኝው የሚያጠናቸዉ ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልዩነት አላቸዉ ብሎ ያገኛቸዉን መረጃዎች በስታቲስቲካዊ ዘዴ አይገልፃቸዉም። /ያለው እንዳወቀ: 2006: 43/

ከዚህ በመነሳት አጥኚው ጥናቱን ለማከናወን አይነታዊ ዘዴን በመጠቀም አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ትንተና ይሰጣል። በዚህም ከአይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም አልተዘዋወረችም ልቦለድን ከገፀ ባህሪያት አሳሳል  አንፃር ትንተና አድርጓል። ገላጭ ምርምር ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናታዊ ፅሁፎችን፣ የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን እና አጋዥ መፅሀፍቶችን በመጠቀም ትንተና እና ጥናት የምናደርግበት የምርምር አይነት ነው።

### 1.7.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ በዋነኝነት የሚጠቀምበት መንገድ የመዝግቦት ፍትሻ (Document review) በመጠቀም መረጃዎችን የሚሰበስብ ይሆናል። የመዛግብት ፍተሻ(Documen review) አንድን ጥናታዊ ፅሁፍ በትክክል መረጃዎችን ከተለያዩ አጋዥ መፅሀፍቶ፣ ድህረ ገፆች እና የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎችን በመቃኘት መረጃዎችን የምንሰበስብበት ዘዴ ነው።

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አደረጃጀት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አብይ አላማ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የጥናቱ አደረጃጀት እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ይዳስሳል። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳ ድርሳናት፣ የገፀ ባህሪያት ምንነት፣ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ምንነት፣ አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል፣ ማህበራዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል፣ ስነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል፣ ሞራላዊ የገፀ ባህሪያት ምንነትንና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝትን ዳስሷል። በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና፣ የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክና አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ትንተና አድርጓል። በምዕራፍ አራት ደግሞ መጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦችን አቅርቧል።

## 1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ ጥናት ስራ ወቅት ያጋጠሙ ጉልህ ሊባሉ የሚችሉ ችግሮች አጥኝው የጊዜ ማነስ ፣ በታቀደላቸዉ የጊዜ ወሰን መረጃ አለማግኘት፣ በቂ የሆኑ መጽሃፍትን አለማግኘት፣ በቀጥታ የሚገናኝ ተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፍ አለማግኘት መጠነኛ ችግሮች ሆነዉ ይጠቀሳሉ።

### 1.9.1. ለችግሮቹ የተወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦች

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ለነበረዉ ችግሮች አጥኝው የወሰደዉ የመፍትሂ ሃሳብ በአማካሪው በመታገዝ ከአጥኝው ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥናታዊ ፅሁፎች ለማግኘት ችሏል። ሌላዉ በተቻለ መጠን የመውጫ ፈተና ዝግጅቱን ቀንሶ ቀን ከሌት በመስራት እና ጊዜውን በአግባቡ በመጠቀም በጊዜዉ ለማደረስ ችሏል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የገፀ-ባህሪያት ምንነት

ገፀ-ባህሪ ማለት የሥነ-ፅሁፍ ዘርፎች ላይ ደራሲው ሊናገረው የፈለገውን ታሪክ ወክሎ የሚመጣ ነው። ይህ ገፀ-ባህሪም ውጫዊና ውስጣዊ ስብዕና የተሸከመ ሲሆን ሰው፣ እንስሳ፣ ግውዝ ወዘተ ማንኛውም ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ ታሪኩ በእነማን ይነገራል? እነማን አሉበት? በሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጠን በገፀ-ባህሪው ነው። የዘሪሁን አሰፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን" በሚለው መፅሀፉ ስለ ገፀ ባህሪያት እንዲህ ሲል ያጠናክርልናል።

> በአንድ ልቦለድ ውስጥ የሚተረክ ታሪክ
>
> የማን ነው? የሚል ጥያቄ ሲጠየቅ መልሱ
>
> በቀጥታ የእገሌ ታሪክ ነው። የሚል ይሆናል
>
> እና እገሌ ተብሎ የሚጠቀሱት ደግሞ የተለያዩ
>
> ባህሪትና የህይወት ገፅታወች ያሏቸው ሰወች
>
> ናቸው። /ዘሪሁን አስፋው፣ 2005፣160/

ከላይ ከተጠቀሰው ሃሳብ እንደምንረዳው ገፅ-ባህሪ ማለት በልብወለድ የሚነገር ታሪኩ የማነው? ሲባል የአበበ፣ የአማኑኤል፣ የዮሐኒስ ወዘተ ነው ሊባል ይችላል። ይህ መሆኑ ደግሞ ወይም በታሪኩ ውስጥ እነርሱ መገኘታቸው ገፀ-ባህሪ የሚል ስያሜ ይሰጣቸዋል። እንዲሁም ገፀ-ባህሪያቶችን ለመለየት የተለያየ ማንነት ተሰጥቷቸው በልቦለድ ወይም በተውኔት ውስጥ በተፈጠረላቸው አለም ላይ እየኖሩ ታሪክን የሚያስቀጥሉ የተለያዩ ፍጡራን ናቸው። ፈንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መጽሀፉ ገፀ-ባህሪያትን እንዲህ በማለት ገልፆልናል።

> ገፀ ባህሪ በጣም ጠቃሚ ከሚባሉት ከተውኔት አላባውያን (አላባዎች)
>
> አንዱ ነው። ገፀ ባህሪ የሚለው ቃል በፈጠራ ታሪክ ውስጥ ያሉትን
>
> የድርሰቱን ሰዎች (አበበ፣ ከበደ፣ አልማዝ) በድርሰቱ ውስጥ የተሳሉትን
>
> እንስሳት (አህያ፣ ጅብ፣ በግ፣ ቀበሮ) በተውኔታዊ ታሪክ ውስጥ የሚቀረፁ
>
> ትን ሰማያዊ ወይም ሀተታ ተፈጥረሯዊ ፍጥረታትና መናፍስት (ሰይጣናት፣

መላዕክት፣ ሠናይ መናፍስት እኩይ መናፍስት፣ እኩይ መናፍስት፣ ጣእረ መንፈስ) እና እረቂቅ ሀሳቦች (ተንኮል፣ ደግነት፣ መልካም ስራ፣ ቁንጅና) የመሰሰሉትን ይወክላል። ገፀ ባህሪያት በገሃዱ አለም ፍጡራን አካል እና አምሳል ተለክተው የሚቀረፁ የልቦለድ፣ የተውኔት፣ የተራኪ ግጥም፣ በጥቅሉ የፈጠራ ስራ ሰዎች ናቸው። /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፣25/

ይህ ማለት እንደ ተፈጠረው ታሪክ የሚለያዩ ሰውኛ ማንነት እና ገፅታ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ከዚህ ውጭ በሆነ መልኩ በእንስሳት፣ ሰዋዊም ሆነ ተፈጥሯዊ፣ መናፍስት እንዲሁም ረቂቅ ሀሳቦች ሆነው ይቀርባሉ። ታዲያ እነዚህን ነገሮች መስለውና ወክለው የመጡት አካሎች ገፀ–በህሪያት ናቸው ማለት ነው። በአጠቃላይ በፈጠራዊ በሆነ ስራም ሆነ ፈጠራዊ ባልሆነ ስራ ውስጥ ታሪኩን ለመንገር የሚመጡ ፍጥራን ገፅ–ባህሪ ይባላሉ። ብቻ የመጡት ገፀ–ባህያት በአንባቢወችም ሆኑ በተመልካቾች ዘንድ ሲታዩ ለወከሉት ነገር በሚገልጽና በሚያሳውቁት መልኩ ውጫዊ ገፅታቸውን እንዲሁም ውስጣዊ ማንነታቸውን በደንብ ተገልፆ ቢቀመጥ የሚመረጥ ይሆናል ወይም የተሻለ ነው እንዲሁም ገፀ ባህሪ ማለት ደራሲው በፈቀደላቸው የህይወት ውጣ ውረድ የሚንቀሳቀሱ በእውኑ አለም ውስጥ የሌሉ ግን መስለው የልቦለዱን ታሪክ የሚቋጩ የፈጠራ አለም ሰዎች መሆናቸውን ያስረዳናል። በተጨማሪም ገፀ ባህሪያት በስነ ፅሁፍ ውስጥ ብዙ ትርጉሞች እንዳሉት ሀረሽው "የስነ ፅሁፍ ቃላት ትርጉም" በሚለው መፅሀፉ ገልፆታል "ገፀ ባህሪ በስነ ፅሁፍ ውስጥ አያሌ የታወቁ ትርጉሞች ይኖሩታል። ከነዚህ ዋነኛው በታሪክ፣ በልቦለድ፣ በተውኔት፣ ወዘተ ውስጥ የተወከለ ሰው ነው።"/1972፣71/

## 2.2 የገፀ–ባህሪ አሣሣል ምንነት

ገፀ-ባህሪያት ደራሲው እንደ መሳሪያ ሊጠቀምባቸው የፈለገውን እና ዕውናዊ ያልሆኑትን እውናዊ አስመስሎ በመረጠው መልኩ ማቅረብ ይችላል። ሲያስቀምጣቸው ግን የባህሪ አሳሳላቸውን አካለዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ሞራላዊ የአሳሳል ሁኔታቸውን ለተደራሲያን ግልፅ ይሆኑ ዘንድ ሳይበረዝ፣ ሳይከለስ ቁልጭ አድርጎ ማስቀመጥ አለበት። ደራሲው ጥናት አድርጎ የሚያበለፅጋቸው ወይም የሚያመጣቸው ገፀ ባህሪያት የአነጋገር ለዛቸውን እንዲሁም አስተሳሰባቸውን ሁሉ በደራሲው ምናብ የሚበለፅጉ ናቸው። ይህንን አስመልክቶ ፋንታሁን እንግዳ ‘’የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ’’ በሚለው መፅሀፍ ላይ እንደሚከተለው አስቀመምጦታል፡-

ገፀ-ባህሪ የተናጠል ድርጊት፣ የአነጋገር ልምድ እንቅስቃሴ፣

> አስተሳሰብ፣ በታሪካዊ ተውኔት በደራሲው ፈጠራ የሚዳብሩ
> ናቸው። ከደራሲው ምናብ የሚመነጩት አላባዎችም ከተነሳው
> ታሪካዊ አገባብ ሊያፈነግጡ አይገባም። /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፣ 99/

በዚህም መሰረት አንድ ልቦለድ ሌላም የስነ ፅሁፍ ስራ ደራሲው ታሪኩን በሚፅፍበት ጊዜ የገፀ-ባህያሪት አሳሳል ላይ ጥንቃቄ የግድ ይለዋል። በተጨማሪም መጠቀም የሚገባው የምናብ ፈጠራዎች በማስተዋል መለየት መቻል ይኖርበታል።

ገፀ–ባህሪዎች እንደየ ልቦለዳዊ ዘውጎች ቢለያዩም ተስለው ሲቀርቡ ግን ለተደራሲያን ተደርሰው ለሚመጡላቸው ገፀ–ባባህሪያት በእውነተኛው አለም ላይ አሉ ብለው እስኪያምኑ ድረስ በጥንቃቄ ተስለው መቅረብ ይኖርባቸዋል ማለትም ማንኛውም ሰው በሂወቱ የሚያከናውነውን ድርጊት የሚያደርጉ በመሆኑ ከእውኑ አለም ፍፁም የተለዩ እንዲሆኑ አይፈለግም። ከእውኑ አለም ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት እንዲኖራቸው ከተፈለገ ደግሞ በአራቱም የገፀ ባህሪያት አሳሳል ማለትም ከማህበራዊ፣ ከአካላዊ፣ ከሞራላዊ እና ከስነ ልቦናዊ አሳሳል በመመስረት ገፀ ባህሪያቶች ቢሳሉ ይመረጣል። ፈንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፉ የአጥኚውን ሃሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክራል።

> በተውኔትና በልቦለድ እንዲሁም በሌሎች የፈጠራ ስራወች
> የሚቀረፁ ገፀ ባህሪያት ማንነት ይበልጥ የሚታወቁበት
> ከንግግራቸው ይልቅ በስራቸው ወይም በተግባራቸው ነው።
> ገፀ ባህሪያቱ ብልጠታቸው፣ አስተዋይነታቸው፣ እምነታቸው፣
> ሰብዓዊነታቸው፣ ጭካኔያቸው ሌላም የተባለ ፀባያቸው ሁሉ
> በተግባራቸው አማካኝነት እነሱነታቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳ
> የናል። የገፀ ባህሪ አሳሳል በድርሰቱ ታሪክ አንዱን ድርሰተሰብ ከሌ
> ላው ለይተን ለማስቀመጥ የምንገልፅበት ዘዴያችን ነው።
>
> /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፤34-35/

ገፀ–ባህሪያት የባህሪ ዘላቂነት እንዲኖራቸው የተወሰደውን ጥቅስ ያሳየናል። ለምሳሌ አንድ ገፀ–ባህሪ የመወደድና የመጥላት ስሜት ኖሮት የሚወደውና የሚጠላው ነገር ተለይቶለት ይታያል። ታድያ ይህ ባህሪው እያገላበጠ የሚጠላውን ነገር ሲወድ የሚወደውን ነገር ደግሞ ሲጠላ ከታየ የባህሪ ዘላቂነት አይኖረውም በመሆኑም ዘላቂነቱ እንዲኖር የሚወደውን ነገር እስከፍፃሜው

እየወደደ የሚጠላውንም ልክ እንደዘው እስከ መጨረሻው እየጠላ መታየት አለበት ይህ ሲሆን ደግሞ በውጫዊው መልካቸው በተጨማሪም በውስጣዊ በሆነ መልካቸው በውል መታየት አለበት። በእነዚህ ሁለት አብይት የገፀ–ባህሪ አሳሳል ውስጥ የሚገኙ ነጥቦችም በዝርዝር እየተለዩ ሊገለፁ ይገባቸዋል።

በአጠቃላይ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ዘዴዎች በአራት ይከፈላሉ። እነሱንም በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

### 2.2.1 አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል

በዚህ አሳሳል ደረጃ ገፀ ባህሪያትን የምንለያቸው በአካላዊ ገፅታቸው ነው። ለምሳሌ ረጅም፣ አጭር፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ወፍራም፣ ቀጭን ... ወዘተ ብለን የምንጠራቸው ማለት ነው። ታድያ ይህ የአሳሳል አይነት ብዙ ጥረትን የማይጠይቅ ልበለዱ ወይም ጽሁፉ ለተደራሲያን እንዲመችን አድርገን የምንስለው በዚሁ የአሳሳል ደረጃ ነው። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፉ የአጥኝውን ሀሳብ እንዲህ በማለት አጠናክሮታል።

> ገፀ ባህሪያት ከምንም በፊት ምንነታቸው ለአንባቢም ሆነ ለተመልካች ይፋ የሚሆ ነው በመጀመሪያ የገፀ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃ ማለትም በነፍስ ወከፍ አካላዊ አቋማቸው ገለፃ አማካኝነት ነው። በዚህ የአሳሳል ደረጃ የእያንዳንዱ ገፀ ባህሪ አለባበስ፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ እንቅስቃሴ፣ ጤና፣ ድምፅ፣ መልክ ማለትም ጥቁረት፣ ንጣት፣ ጠይምነት፣ አቋምን፣ ማለትም ውፍረት፣ ቅጥነት፣ እርዝመት፣ እጥረት፣ ምን እንደሆነ ይብራራል። የገፀ ባህ ሪያት አካላዊ ገለፃ ብዙ ጥበብን የሚጠይቅ አይደለም። ልክ በመንገድ ከሚተ ላለፉት ሰዎች የአንዱን አቋም ተመልክተን ከምንናገረው የተለየ አይደለም። በዚህ ምክንያት ታዲያ የገፀ ባህሪያት የመጀመሪያ ደረጃ አሳሳል ማለትም የአካላዊ አቋ ማቸው ቀረፃ በጣም ቀላሉ የገፀ ባህሪያት አሳሳል አይነት ተደርጎ ይወሰዳል።
>
> /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፤27

ይህ ማለት የገፀ–ባህሪው ውጫዊዉ መልክ ምን ይመስላል? የሚለውን ነገር በሚመልስ መልኩ ተብራርቶና ተገልፆ በተለያዩ የአገላለፅ መንገዶች በመጠቀም ሊገለፅ ይገባል። ይህ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በተደራሲያን ዘንድ እገሌን ይመስላል እገሌ ነው ብለው በአይምሯቸው ገፀ–ባህሪውንም

ከሌሎች ገፀ–ባህሪያት በመልኩ፣ በአቋሙ(አጭር እና ቀጭን) መሆኑን እንደለዩት ይረዳቸዋል። በአጠቃላይ ገፀ–ባህሪዎች ያላቸው አካላዊ ምንነት ሊገለፅ ይገባል።

### 2.2.2 ማህበራዊ ገፀ ባህሪያት አሳሳል

ከስሙ እንደምንረዳው ይህ አይነት የአሳሳል ደረጃ የሚያተኩረው ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነው። ገፀባህሪው ያለበትን ደረጃ ያሳየናል ለምሳሌ ተምሯል አልተማረም፣ አግብቷል አላገባም፣ የሀይማኖት ሁኔታውስ ምን ይመስላል ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር ያለው ተግባቦት ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንዴት ነው የሚሉትን ያጠቃልላል። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ በማለት የአጥኚውን ሀሳብ ያጠናክራል።

> ይህንን የተወሳሰበ ማህበራዊ ግንኙነት ለማወቅ በመንገድ
>
> ስንሄድ ተመልክተን በእርዝመታቸው እና በእጥረታቸው ወይም
>
> በሽምግልናቸው እና በወጣትነታቸው እንደምንፈርጃቸው ሰዎች
>
> (ገፀ ባህሪያት) ልንገነዘባቸው መሞከሩ ከቶ የማይቻል ነገር ነው።
>
> ስለሆነም እያንዳንዱን ገፀ ባህሪያት ማህበራዊ ግንኙነት ለማወቅ
>
> የግድ ወደ ተውኔቱ ታሪክ ጠልቆ መግባት ያስፈልጋል። በዚህ
>
> በማህበራዊ ግንኘነት ቀረፃ ከሚካተቱት ሌሎች ነጥቦች መካከል
>
> እንደ የጋብቻን እና የላጤነትን ህይወት፣ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማት
>
> ያለውንተሳትፎ፣ ሃብታምነት እና ድህነት፣ ሃይማኖቱ እና የፖለረቲካዊ
>
> አቋም፣ የተሰማሩበት የሙያ መስክ ወይም ዘርፍ የመሳሰሉት ይገኛሉ።
>
> /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፤28/

ገፀ–ባህሪው ታሪኩ ውስጥ ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር በምን በምን ጉዳዮች ላይ ይገኛል በእድር፣ በሰርግ፣ በተስካር ወይንም ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያምንበት ና እሚከተለው ሀይማኖት እንዳለው አልያም እንደሌለው ህይወቱስ እንዴት ነው እሚመራው ትዳር መስርቶ ነው ሳይመሰርት የኑሮ ደረጃውስ ምን ይመስላል የሚሉትን ነገሮች በጥልቀት የሚገለፁበት ቦታ ነው። በመሆኑም ማህበራዊ አሳሳላቸው በዚህ መልክና በዚህ መሰረት ሊገለፅ ግድ ይላል ወይም ይገባል።

## 2.2.3 ስነ ልቦናዊ ገፀ ባህሪያት አሳሳል

ሶስተኛው ነጥብ ሥነ-ልቦናዊ የገፀ ባህሪ አሳሳል ነው። በዚህ ውስጥ የሚጠቀሱት የገፀ-ባህሪውን ረቂቅ ሃሳቦች ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ትኩረቱን የሚያደርገው ገፀባህሪው በውስጡ ስለሚመላለሱ ወይም ስለሚያስባቸው ጉዳዮች ነው። ፋንታሁን እንግዳ ስለ ሰነ ልቦናዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ" በሚለው መፅሃፉ የአጥኝውን ሀሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክራል።

> ስነ ልቦናዊ የአሳሳል ደረጃ የሚያተኩረው የገፀባህሪያትን ልዩ
>
> ልዩ ምኞቶች፣ ተስፋዎች የመጥላትና የማፍቀር ስሜቶችን እና
>
> ሰበበ ድርጊቶች በድምሩ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው
>
> ለውጫዊ አለም የሚሆኑትን ስሜታዊነትንና አስተዋይነትን ሁሉ
>
> በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ
>
> ነው። /ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፣28/

ገፀባህሪ በዚህ አይነት የአሳሳል ደረጃ ሲሳል ውስጡ ያሉትን ስሜቶች ወደ ተመልካች ማሳየት የሚችልበት መንገድ መፍጠር አለበት። ይህ ማለት የተሳሉት ገፅ-ባህሪያት ምኞት እምያበዛ ፍላጎቶቹን ለማሳካት በመመኘት ይህ ነገር እንደዚህ ሆኖ ባየሁት እንዲህ በተደረገልኝ እያለ የሚመኝ ነው ወይስ በራሱ ጥረት እየተጠቀመ ከሱ በላይ የሆኑትን ነገሮች የራሱን ጥረት እያደረገ ለበላይ ለሆነ ነገር ተስፋ እያደረገ በተጨማሪም የሚወደውና የሚጠላው ነገር እየተለየለት መሳል ያለበት በስነ-ልቦናዊ የገፀ-ባህሪ አሣሣል ነው።

## 2.2.4 ሞራላዊ ገፀ ባህሪያት አሳሳል

ሞራላዊ አሳሳል ላይ የገፀ-ባህሪው የክብር ጉዳይ ምን እንደሚመስል የምናይበት ነው። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፉ ሞራላዊ የገፀ ባህሪ አሳሳልን እንዲህ ሲል አብራርቶታል።

> ተፈጥሮ ከሚፈቅደው በታች ወርደ ቅጥ ያጣ ስግብግብ
>
> ሆኖ ሲቀርብ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ
>
> ሲገኝ፣ ወይም ከሁለቱም በተቃራኒ አለማዊ እና መንፈሳዊ

መመርያዎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪ እና ሰባኪ ሲሆን

በሚያሳዩ እና በመሳሰሉት ፍሬ ሀሳቦች ላይ በማተኮር ገፀ

ባህርያትን ከዚህ አንፃር በመቅረፅ ላይ ያነጣጥራል።

/ፋንታሁን እንግዳ፣ 2005፤29/

ይህ ማለት ተስሎ የመጣውን ገጸ-ባህሪ ክብር ፈላጊ ሆኖ ክብሩን ለማስጠበቅ ደግሞ በሚያደርጋቸው ድርጊቶቹ ክብረ ቢስ መሆኑ ከሚገባው በታች ውርደተኛ እንደሆነ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊነቱ በዝቶ ለግላዊ ክብሩ የሚጨነቅ አልያም ከዚህ ውጭ እውነታዎች እና ምክኒያዊነት/logical/ በመቀበል ሃይማታዊ እሳቤወችም ሳይለቅ ሁለቱም በማጣመር ክብሩም የሚገባውን ያህል ብቻ አስከብሮ የሚኖር ነው ወይ ለሚል ጥያቄ መልስ የሚሆነው ከእነዚህ ሶስት ነገሮች የተውኔት ታሪኩን ከሚፈቅደው አንዱ ተስቶት ሊሳል ይገባል።

## 2.3 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

አጥኚው ጥናቱን በሚያካሂድበት ወቅት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ከገፀ ባህሪያት አንፃር የሚተነትን ጥናታዊ ፅሁፍ ባያገኝም ተያያዥነት ያላቸውን ጥናት እንደመነሻ ለማንበብ ሞክሯል። አበባው አበበ በ2014 "ቴሎስ ረጅም ልብ ወለድ ከልብ ወለድ አላባውያን አንፃር" በሚል ርእስ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ኦፍ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ቃኝቷል። አጥኚው የራሱ ጥናታዊ ፅሁፍና ሌላኛው ጥናታዊ ፅሁፍ ያላቸውን አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ያቀርባል።

### ተመሳሳይነት

ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከልቦለድ አለባውያን አንፃር መጠናቱ ገፀ ባህሪም ከልቦለድ አላባዎች አንዱ በመሆኑ ሁለቱም ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ትንተና ያደረጉበት መንገድ ያመሳስላቸዋል። በተጨማሪም ሁለቱም የመረጡት የአጠናን ዘዴ አይነታዊ የምርምር ዘዴን መጠቀማቸው ሁለቱም ጥናታዊ ፅሆፎች ያመሳስላቸዋል። በመጨረሻም ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች በአራት ምዕራፎች የተዋቀሩ ናቸው።

### ልዩነቱ

አጥኝው ከሚያጠናው ጥናት የሚለየው ደግሞ ይህ ጥናት "አልተዘዋወረችም ልልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ብቻ ትንተና ማድረግ ሲሆን ያኛው ደግሞ ሰባቱንም የልቦለድ አላባውያንን የሚተነትን በመሆኑ አንዱ ልዩነታቸው ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የመረጃ ትንተና

### 3.1.1 የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

አልተዘዋወረችም ልቦለድ በደራሲ አሌክስ አብርሃም ተደርሶ በ2016 ዓ.ም በኤ..ማተሚያ ቤት ታትሞ ለአንባቢያን የቀረበ ሲሆን ልቦለዱ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ እና በውስጡም 239 ገፆችን የያዘ ነው። ይህ ልቦለድ አራት ዋና ዋና ገፀ ባህሪያት ያለው ሲሆን አራቱም ገፀ ባህሪያት ከዚህ በፊት ስላሳለፉት የህይወት ውጣ ውረድ ወይም ግለ ታሪካቸውን እያንዳንዳቸው የሚገልፁበት ልቦለድ ነው። ታሪኩ የሚጀምረው አብርሀም ጀልነቱ እና ዝመተኛነቱ ከምን የመጣ እንደሆነ ግራ እስኪገባው ድረስ እየገለፀ ነው። የአካባቢው ማህበረሰብ እና የቅርብ ጓደኞቹ የአብርሃምን ስም ለማጥፋት ነቀፌታ ያዘለ ንግግርና የፈለጉትን ስም ይሰጡታል። አብርሃም የኘካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠው ሰም ሀሰት ቢሆንም አንድም ቀን ለማስተባበል ሞክሮ አያውቅም። አብርሃም አሁን ላይ ሰለ ማህደረ ሰላም ባሰበ ቁጥር ከራሷ አስበልጣ ትወደው ሰለነበር እና ያጣትም በራሱ ጅልነት በመሆኑን አብዝቶ ይፀፀታል። አብርሃምና ማህደረ ሰላም አራት አመታት በፍቅር አብረው ቆይተዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀጣጥረው የተገናኙት ቅዳሜ ቀን ከሜክሲኮ ወዲ ቄራ በሚወስደው መንገድ ከገነት ሆቴል ከፍ ብሎ የሚገኝ አንድ ሬስቶራንት ነበር። ከዚያ ወዲህም ማህደረ ሰላምና አብርሃም የልብ ፍቅረኛሞች ሆኑ። እዚህ ሬስቶራንት ላይ አዘውትረው ፒዛ ይበሉ ነበር። ማህደረ ሰላም አብርሃም ከብዙ ሴቶች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ብታውቅም ከልቧ ስለምትወደው ላለፉት ታሪኮቹ ግድ ግድ አይሰጣትም። ማህደረ አስቸኳይ ሰራ ብትይዝም አብርሃም በደወለላት ቁጥር ሁሉንም ጥላው ትሄዳለች። በስራ ምክንያት ከከተማ ካልወጣች ሁልጊዜ በተቻለ ፍጥነት አብርሃም ጋር ሳትደርስ የትም አትሄድም። ማህደረ ሰላም አብርሃም ቤት ያለውን ሲዲ ፕሌየር አብዝታ ተወደው ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ማህደረ ሰላም አብርሃም እንዲያገባት ትጠይቀዋለች። አብርሃምም አገባሻለሁ ከሚል ቃል በስተቀር ቃሉን ጠብቆ አላገባትም። የማህደረ ሰላም አባት ልጃቸው አግብታ የልጅ ልጅ ማየት ስለሚፈልጉ ባል እንድታገባ ይጎተጉቷታል። ማህደረ ሰላም አባቷን ለማስደሰት ብላ ከሁለት ሳምንት በኋላ ዮናስ ከሚባል ከአሜሪካ የመጣ ሰው ጋር ልታገባ መሆኑን ለአብርሃም ትነግረዋለች። አብርሃም በውሳኔዋ ተደናግሮ ችግሩ የራሱ እንደሆነ በመገንዘብ ድንግዝግዝ ብሎ ሰውነቱንም ሆነ ስሜቱን ማዘዝ ይሳነዋል።

ከሁለት ሳምንት በኋላ የሰርጓን ዝግጅት ጨርሳ ፀጉሯን ተሰርታ ሚዜዎቿን በኮንትራት ታክሲ ትታ መጥታ የሰርጓ ዋዜማ ከአብርሃም ጋር ትተኛለች። ማህደረ ሰላም በትዳሯ ደስተኛ ባትሆንም ዮናስን አግብታ ስራዋን ለቃ የቤት እመቤት ሆነች። ከዚህ በኋላ ከማህደረ ሰላም ጋር ለአንድ አመት ያክል በአካልም ሆነ በስልክ ተገናኝተው አያውቁም። ከሶስት አመት በኋላ ቦሌ አድናሞል ሆቴል በሚባል ህንፃ ላይ ማህደረ ሰላም ከመጠን በላይ ወፍራ ከአንድ ህፃን ልጅ ይዛ ያያታል። አሁን ላይ ማህደረ ሰላም አንድ የሁለት አመት ሴት ልጅ እና ሁለተኛ ልጅ አርግዛ በመጠባበቅ ላይ ናት።

ሀይማኖት በመልከ ጥፉነቷ የበታችነት ስሜት እና ፈጣሪን አብዝታ ትወቅሳለች። ከእለታት አንድ ቀን ታክሲ ውስጥ ገብታ በምትጓዝበት ጊዜ ቶማስ የተባለ ወጣት ጥርሶቿ እንደሚያምር ይነግራታል። ሀይማኖት አንድም ወንድ እንደዚህ ብሏት ስለማያውቅ በቶማስ ንግግር ደስ ብሏት ተዋውቀው ስልክ ተቀያይረው ይለያያሉ። ከዚያ በኋላም የልብ ፍቅረኛሞች ባይሆኑም አብረው መዳዝ እና አብረው መተኛት ጀመሩ። የማህደረ ውድቀት ለሀይማኖት ትልቅ ድሏ ነበር። አሁን ደግሞ ማህደረ ዮናስን በማግባቷ ሀይማኖት አብዝታ ትቀናባታለች። ቶማስ መጠጥ ቤት ውስጥ ባልታሰበ ግርግር ሽጉጥ ተተኩሶበት ይሞታል። ሀይማኖት ፍቅረኛዋን በሞት ብትነጠቅም ብዙም ሀዘን አልታየባትም ነበር።

ዮናስ ሁለት እህቶች እና እናት ያሉት ሲሆን ቤተሰቦቹን ከራሱ አስበልጦ ይወዳቸዋል። አባቱን በወጣትነት እድሜው ያጣው ሲሆን አባቱ ከሞተ በኋላም ድህነትን ለማሸነፍ ሲል በህገ ወጥ መንገድ ተሰዶ ከህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ጋር ተጋጭቶ መሀል መንገድ ላይ ትተውት ሄደው በእስር እና በስቃይ ብዙ ችግሮችን አሳልፏል። አሁን ላይ ያሳለፋቸውን የስቃይና የመከራ ጊዜያቶች ባስታወሰ ቁጥር ሰሜቱ ክፉኛ ይጎዳል። ከአስራ ሰባት አመት የስደት ጊዜ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ማህደረ ሰላምን አግብቶ ኑሮን እንደገና 'ሀ' ብሎ ጀመረ።

## 3.1.2 የገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና

በዚህ ልቦለድ ውስጥ ብዙ ገፀባህሪያቶች የሚገኙ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ ከተመረጡ ገፀ ባህሪያቶች ላይ ማለትም ዋና ገፀ ባህሪያቶችን የምንመለከት ይሆናል። የዚህ ልቦለድ ዋና ዋና ገፀ ባህሪያቶች እነዚህ ናቸው አብርሃም፣ ማህደረ ሰላም፣ ሃይማኖት እና ዮናስ ናቸው።

### 3.1.2.1 የአብርሀም አካላዊ አሳሳል

አብርሀም ከአካላዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ አንፃር ሲታይ ስለ እድሜው በግልጽ ባይገለፅም በ30ዎቹ የእድሜ ክልል አካባቢ ይደርሳል ብሎ ለመናገር ያስደፍራል፡፡ ቀይ የቆዳ ቀለም ያለው፣ ሞላ ያለ ጺም ያለው መልከ ቀና እና መካከለኛ ተክለ ቁመት ያለው መሆኑን በማህደረ ሰላም አንደበት ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ አብረሃም ደራሲ እንደመሆኑም መጠን የሚለብሳቸው ልብሶች ሱፍ፣ ንፁህ ልብሶች እና ሸሚዞችን ያዘወትራል። ለማስረጃነት መፅሃፉ ውስጥ ስለ አብረሃም ማህደረ ሰላም ለመጀመሪያ ጊዜ ስታየው የተናገረችውን ንግግር እንመለከታለን።

"ፕሮግራሙ ወደማለቂ ሲቃረብ ወጣት እና ንፁህ ልብስ የለበሰ በስርዓት ፂሙን የተስተካከለ ልጅ ወዴ መድረክ ሲወጣ "እሱ ነው" አለችኝ። ሰው እንደዚያ አፍጥጬ አይቼ አላውቅም። ትልቅ ሰውዬ ነበር የጠበኩት፣ መላጣ መነፀር የሚያደርግ ምናምን።"(ገፅ፣ 82)

ከዚህ እንደምንረዳው አብርሀም መካከለኛ ተክለ ቁመና ያለው፣ ወጣት መሆኑን፣ በአለባበሱም ንፅህናውን የጠበቀ ልብስ እንደሚለብስ ያስረዳናል።

### 3.1.2.2 የአብርሃም ማህበራዊ አሳሳል

አብርሃም ማህበራዊ አሳሳሉ ያላገባ፣ ሴቶችን ቀን በቀን የሚቀያይር እና በመፅሀፍ ምርቃት ቀን እንዳጋጣሚ ከተዋወቃት ከማህደረ ሰላም ጋር አራት አመታት ያክል በፍቅር አብሮ ቆይቷል። እንደማስረጃነትም ከመፅሀፉ ላይ የሚከተሉትን ንግግሮች እንመለከታለን።

"ለአራት አመታት "በፍቅር" ቆየን። ከልጅነት መፍለቅለቅ ወዴ አዋቂነት መብሰልሰል የደረሰችው በእኔ ላይ ነው።

"አራት አመት ብዙ ነው፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናት ተወልደው በየ ልሳናቸው መናገር ጀምረዋል፤ መናገር መጀመር ቀላል አይደለም።"(ገፅ፣ 7)

ከዚህ እንደምንረዳው አብረሃም እና ማህደረ ሰላም አራት አመታት አብረው መቆየታቸውን እና የመጀመሪያ ፍቅረኛዋ መሆኑንም ገልፆልናል።

ከማህደረ ሰላም ጋር ከተለያዩ በኋላ ከተለያዩ ሴቶች ጋር ቢገናኝም ከስሜታዊ ፍላጎቱ ውጭ ምንም አይነት የፍቅር ግንኙነት አልጀመረም። ይህንንም እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ የተወሰኑትን ንግግሮች እንመለከታለን።

"ጨራርሰው ስለነበረ፤ ባሏ የወንበር መደገፊያው ላይ ያንጠለጠለውን ጃኬት ሊያነሳ ዞር ሲል፤ የሆነ ነገር አለችውና መልሶ ተቀመጠ። አስተናጋጇን በምልክት ጠርታ ቡና አዘዘችው፤ ከሩቅ በከንፈራ እንቅስቃሴ ነው ቡና ማዘዟን ያወኩት "ቡና" ስትል ውብ እንደሚያፏጭ ሰው ስብስብ ብሎ በትንሹ ከፈት አለ፤ ማሂ ሰላም ቡና አትወድም፤ ለመቆየት እና የቀጠርኳትን ሴት ለማየት እንደፈለገች ገብቶኛል። ስልኬን አወጣሁ እና የቀጠርኳትን ልጅ ይቅርታ ጠይቄ የቀጠሮውን ቦታ ቀየርኩት።"(ገፅ፣ 48)

ከዚህ እንደምንረዳው ማህደረ ሰላም ባለቤትዋ ዮናስን ለመጀመሪያ ጊዜ አብረሃም እና ማሂ ሰላም የተዋወቁበት ሆቴል ይዛው ሄዳ በአጋጣሚ ደግሞ አብረሃም የቀጠራትን ሴት ቀድሞ ተገኝቶ ለመጠበቅ ሬስቶራንት ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ማህደረ ሰላምን ከባሏ ጋር ያገኛታል። ከአብረሃም ንግግር እንደምንረዳው እስካሁ ድረስ ያላገባ መሆኑን እና የቀጠራ ሴት ባለቤቱ እንዳልሆነች ይገልፅልናል።

ስራውም ደራሲ እና በፊት በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ እንደነበረ ይገልፃል። እንደማስረጃነት ስለ ስራው ከመፅሃፉ በአብረሃም አንደበት የተገለፀውን እንመለከታለን።

"በአንድ ፀሃያማ ቀን (ቅዳሜ ቀን መሆን አለበት...ያኔ በአንድ የግል ድርጅት ተቀጥሬ እሰራ ስለነበር ሰው የምቀጥረው ቅዳሜ ቀን ነበር) ከሜክሲኮ ወዴ ቄራ በሚወስደው መንገድ፣ ከገነት ሆቴል ከፍ ብሎ በሚገኝ ሬስቶራንት ውስጥ ነበር ቀጠሯችን።"(ገፅ፣ 9-10)

ከዚህ እንደምንረዳው በመጀመሪያ ትውውቃቸው ጊዜ አብርሃም በግል ድርጅት ተቀጥሮ ይሰራ እንደነበረ እና አሁን ላይም ተቀጥሮ ይሰራበት የነበረውን ስራ እንዳቋረጠ በንግግሩ ገልፆታል።

እንዲሁም ብቻውን ኮንደምኒየም ተከራይቶ የሚኖር ግለሰብ ነው። በኢኮኖሚውም በመካከለኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ይገኛል፤ የትምህርት ደረጃው የመጀመሪያ ድግሪውን በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስነ ፅሁፍ የትምህርት ክፍል የጨረ ሲሆን በምን እንደጨረሰ ባይገለፅም ሁለተኛ ድግሪውንም በማዕረግ ተመርቋል። አብርሃም ዝምተኛ በመሆኑ እና ሁልጊዜ በሚቀያይራቸው ሴቶች አማካኝነት በቅርብ ጓደኞቹ እና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት የቀዘቀዘ ነው።

### 3.1.2.3 የአብርሃም ስነ ልቦናዊ አሳሳል

አብርሃም ከማህደረ ሰላም ጋር አራት አመታት አብረው በፍቅር ሲኖሩ በውስጡ በጣም እየወደዳት ነገር ግን አንደበት አውጥቶ "እወድሻለሁ" የሚል ቃል ከአንደበቱ አለመውጣቱ ወይም አንድም ቀን እንደሚያፈቅራት ለማህደረ ሰላም አለመግለፁ አሁን ላይ የሚቆጭበት እና ሁልጊዜም አዕምሮው ላይ እየተውጠነጠነ ስሜቱን ይረብሸዋል። አብርሃም ማህደረ ሰላምን ከሌሎቹ ከሚገናኛቸው ሴቶች አብዝቶ ይወዳታል። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ከዚያ ሰውነቷ ጋር በፍቅር የወደኩ ፍጡር ነበርኩ። አንድ በአንድ የማውቃቸውን እየተውኩ ለአራት አመታት አብሪያት የቆየሁት፣ በሰውነቷ ፍቅር ነው።"(ገፅ፣ 14)

"ከማውቃቸው ሴቶች ሁሉ ቤቴ የወሰድኳቸው ሁለቱን ብቻ ነበር። የመጀመሪያዋ ደግሞ እሷ ነበረች።"(ገፅ፣ 18)

ከዚህ እንደምንረዳው አብርሀም ከዚህ በፊት ከብዙ ሴቶች ጋር ቢገናኝም ከማህደረ ሰላም ጋር ከተገናኙ እና የፍቅር ግንኙነት ከጀመሩ ወዲህ ማህደረን አብዝቶ ይወዳት ስለነበረ ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዳቆመ ያስረዳናል። እንዲሁም ከሚገናኛቸው ሴቶች ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ እቤቱ የወሰዳት ማህደረ ሰላምን ነው፤ ይህም ለማህደረ ሰላም ምን ያክል ፍቅር እንዳለው ማሳያ ነው።

ፀጉሯን ደጋግማ የምትነካካ ሴት አብዝቶ የሚጠላ፣ ጅልነቱን እርሱም አምኖ የተቀበለ፣ ማህደረ ሰላምን ያጣት በራሱ ጥፋት እና ጅልነት ስለሆነ እሷን ባሰባት ቁጥር አብዝቶ የሚፀፀትበት ድርጊቱ ነው። ይህን እንደማስረጃነት ስንመለከት እንዲህ ይላል፦

"እንባዬ ይመጣል፣ የእውነት ማሂ ሰላምን ሳስባት ልቤ ምድጃ ላይ እንደተጣደ ብረት ድስት፤ ክዳኗን እየገፋች የፈላ እንባ ለማትነን የምትታገል ይመስለኛል። በመሄዷ ሳይሆን ፍቅር አጥታ በመሄዷ። ብድር ጠይቃ የለም እንደተባለች ምስኪን እናት፤ ልጆቿ ተርበው እንደሚጠብቋት፤ አንገቷን ደፍታ ተስፋ ካደረገችው ሰው ተስፋ አጥታ እንደተመለሰች እናት።"(43)

ከዚህ እንደምንረዳው አብርሃምና ማሂ ሰላም ከተለያዩ በኋላ አብርሃም ማሂ ሰላምን ባስታወሳት ቁጥር የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማው ሲያዝን እና ሲፀፀት እንመለከተዋለን።

አብርሃም ከማህደረ ሰላም ጋር ተገናኝተው ሲለያዩ ሰማያዊ ቀለም ባላት ታክሲ ተሳፍራ ስትሄድ ማህደረን በመስኮት ሆኖ ይመለከታት ነበር ከዚያ ወዲህም ሰማያዊ ቀለም የመለያየት ምልክት መስሎ ስለሚታየው አብዝቶ ይጠላል። ይህን እንደማስረጃነት ስንወስድ እንዲህ ይላል፡-

"ከግቢ ውጭ አንዲት ሰማያዊ ላዳ ታክሲ ቆማ እየጠበቀቻት ነበር… ገብታ ሄደች…በቃ። ሰማያዊ ቀለም የመለያየት ባንዲራ ይመስለኛል- እስከዛሬ።"(ገፅ፣ 35)

ከዚህ እንደምንረዳው ለመጨረሻ ጊዜ በአብርሃም ቤት ተገናኝተው ሲለያዩ ማህደረ ወጥታ ስትሄድ በሰማያዊ ላዳ ታክሲ ስትሄድ ይመለከታት ስለነበረ ከዚያ ወዲህም ሰማያዊ ቀለም የመለያየት ምልክት ይመስለው ስለነበረ አብዝቶ ይጠላል።

### 3.1.2.4 የአብርሃም ሞራላዊ አሳሳል

አብረሃም ብዙ ሴቶች አፍቅረውት ፍቅራቸውን እንድረዳቸው እና አብሯቸው እንዲኖር ይጠይቁት ነበር እርሱ ግን ሴቶች አፍቅረው ሲሰቃዩ ማየት አስደስቶት አይደለም፤ ይልቁንስ ሴት ልጅ ስታለቅስበት የሚጨነቅና የሴት ልጅ እንባ ጥሩ እንዳልሆነ ያውቃል፣ ግን ለማፅናናት የሚረዳበት መንገድ ከስነ ምግባር የወጣ ነው። ሴቶቹ ሲያለቅሱበት አብሮ በመተኛት ደስታቸው የሚመለስ የሚመስለው በተፈጥሮው ማስተዛዘን የሚባል ነገር ያልተሰጠው ነው። እንደማስረጃነት በመፅሀፉ በእራሱ አንደበት የተገለፀውን እንመልከት።

"የሴት ልጅ እንባ ልቤን ያስጨንቃታል፤ ቀርባኝ ያላለቀሰች ሴት ግን የለችም። የሴት እንባ ጥሩ አይደለም፣ አጉል ቦታ ይጥልሃል የሚሉትን ሟርት ክፉኛ አመልካለሁ። ባለቀስኩ ቁጥር የሰማይ መልአክት ሁሉ ዶማና አካፋ ይዘው የነገ መንገዴን ቆፍረው ሊያበላሹ፣ በእንባዋ እየቀዘፉ የሚፈጥኑ ይመስለኛል።

"ሴቶች ሲያለቅሱብኝ እንባቸውን የማስቆምበት መንገድ የሚመስለኝ አብሮ መተኛት ነበር።"(ገፅ፣ 12)

ከዚህ እንደምንረዳው አብርሀም ሴት ልጅ ስታዝን ወይም ስታለቅስ የማይወድ እነሱንም በአንደበት ለማፅናናት ያልታደለ፣ አብሯት ስለተኛ ከሀዘኗ የምትፅናና የሚመስለው ገፀ ባህሪ ነው።

### 3.1.2.5 የማህደረ ሰላም አካላዊ አሳሳል

ማህደረ ሰላም እድሜዋ በትክክል ባይገለፅም በ30ዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ እንደ አበባ የምትስብ ቆንጆ ይህ ቀረሽ የማትባል የፀይም እንቁ ያያት ወንድ ሁሉ ለራሱ ለማድረግ የሚመኛት ሁሉን አሟልቶ የሰጣት ቆንጆ ወጣት ናት። እንደማስረጃነት ስለ ማህደረ ሰላም ጥይምና እና ቁንጅና ፍቅረኛዋ አብርሃም መፅሃፉ ላይ የገለፀውን እንመልከት

"ፈጥሮ ከጨረሳት በኋላ ጠይም ቀለም ውስጥ በቀስታ ነክሮ ያወጣት ነበር የምትመስለው። ጠይምነቷ፣ በቀስታ ከላይ ከፀጉሯ ስር ወደ ታች፣ ወደ እግሯ ጣቶች የሚፈስ አይነት ነው። የእጇን አውራ ጣት ሰውነቷ ላይ አጥቅሼ ወረቀት ላይ ባሳርፈው ጠይም አሻራ የማገኝ ይመስለኛል። ለዘላለም የማይጠፋ ጠይምነት።"(ገፅ፣ 13)

ይህ ማለት የማህደረ ሰላም ጥይምና እንከን የማይወጣለት እና ምንም አይነት ጠባሳም ሆነ ሌላ ነገር የሌለባት የፀይም ቆንጆ ወጣት መሆኗን ያስረዳናል።

ማህደረ ሰላም ዮናስን ካገባች በኋላ ለእራሷም እስኪገርማት ድረስ በጣም ወፍራ ነበር። እንደማስረጃነት ስለ ውፍረቷ በአብርሃም አንደበት የተገለፀውን ጠቅሰን እንመልከት።

"ይህ በሆነ በሶስት አመት በኋላ ይመስለኛል፣ እዚህ ቦሌ ኤድናሞል የሚባል ህንፃ ላይ ማሂሰላምን ዳግመኛ አየኋት፤አንድት የምታምር ህፃን ይዛ። አይኔን ማመን አልቻልኩም። ያቺ በአዋቂ ቀራፂ የተሰራች የምትመስል ውብ ሴት የለችም፤ የጤና ነው ወይ? እስከምል በማይታመን ውፍረት ተውጣ ነበር! "ወላድ በድባብ ትሂድ ቆንጆ ሞልቷል" ቢባልም የማይደገሙ መልኮች አሉ፤ የሴት ልጅ ውበት እንደ እጅ አሻራ ነው፤ የአንዷ ሴት ውበት ሌላዋ ላይ ፈፅሞ፤ በተለይ የማሂሰላም የሚደገም አይመስለኝም።"(ገፅ፣ 47)

ይህ መለት ማህደረ ሰላም ከመጠን በላይ እንደወፈረች እና ውፍረቷም ያቺ የምታምረዋን ማሂሰላምን እንዳጠፋት ይገልፅልናል። ከዚያ በኋላ የቀደም ልብሶቿ ጠበዋት ሰፋፊ ቀሚሶችን መልበስ ጀመረች።

### 3.1.2.6 የማህደረ ሰላም ማህበራዊ አሳሳል

ማህደረ ሰላም የቤተሰቦቿ የመጀመሪያ ልጅ ስትሆን ከአብረሃም ጋር አራት አመታት በፍቅር ግንኙነት የነበረች አሁን ላይ ዮናስን አግብታ የአንድ ልጅ እናት እና አርግዟ ሁለተኛ ልጇን በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ጥሩ ባል ያላት ባለ ትዳር፣ የአንድት ቆንጆ ልጅ እናት እና ሁለተኛ ልጅ ያረገዝኩ ሴት ነኝ።"(ገፅ፣ 136)

ከዚህ የምንረዳው ማህደረ ሰላም አሁን ላይ ትዳር መስርታ እንደምትኖር፣ የአንድ ልጅ እናት እና አርግዛ ሁለተኛ ልጇን እየተጠባበቀች እንደሆነ ገልፆልናል።

ማህደረ ሰላም በዙሪያዋ ባሉት ሰዎች፣ ቤታቸው አጠገብ ካለው ጋራጅ ቤት ሰውዬ፣ በዙሪያዋ ካሉት ሰራተኞች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላት፣ በኢኮኖሚዋም እራሷን የማትጥል በመካከለኛ የኢኮኖሚ ደረጃ የምትገኝ እና በትምህርቷም የመጀመሪያ ድግሪዋን በአድስ አበባ ንግድ እና ኮሌጅ ተመርቃ ስትጨርስ ሁለተኛ ድግሪዋን ደግሞ በአካውንቲንግ እና ፋይናንስ ተመርቃ በኦድትነት ትሰራ ነበር። እንደማስረጃነት መፅሀፉ ውስጥ በራሷ አንደበት የተናገረችውን እንመለከታለን።

"ተምሪያለሁ። በአካውንቲንግ ሁለተኛ ድግሪዬን ከአድስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይዤ፤ በኦድትነት እየሰራሁ ነበር። የገንዘብ ችግር አልነበረብኝም። የረባ ነገር ባላደርግ እንኳን ለራሴ በምፈልገው ልክ እኖራለሁ።"(ገፅ፣ 59)

ከዚህ እንደምንረዳው ማህደረ ሰላም ከፍተኛ የማዕረግ ተመራቂ መሆኗን፣ በተመረቀችበት የስራ ዘርፍ ተቀጥራ እንደነበረና የኢኮኖሚ ችግር እንደሌለባት ይገልፅልናል። ይሁን አንጅ ዮናስን ካገባች በኋላ የቤት እመቤት ሆና ልጅ ወልዶ ከማጫወት ውጭ ስራዋንም አቁማለች።

መህደረ ሰላም የአባቷ የስለት ልጅ ስትሆን ሀይማኖቷም ኦርቶዶክስ ነው። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ከዚያ በኋላ የሀይማኖት ሰዎችን እና የመንፈሳዊ ወሬ በሩቁ መሸሽ ጀመርኩ። እግዚአብሔር ብየ መጥራት ከበደኝ። በምድር ላይ እንደ እኔ ያለ ሀጢያተኛ ያለ መስሎ እስከማይሰማኝ ራሴን ተጸየፍኩት፣ ጠላሁት። ከሁሉም ልቤን የሰበረው፣ ከህፃንነቴ ጀምሮ አንድ አመት እንኳን አልፎኝ የማያውቅ ልማድ ነበረኝ፣ አባቴ ጋር ሆነን ለጥምቀትየልደታን ታቦት መሸኘት "ለልደታ ሴት ልጅ ከሰጠሽኝ በየዓመቱ ላንቀር ብየ ተስያለሁ" ይላል የአንድ አመት ልጅ ሆኘ ነው አቅፎ የወሰደኝ፤ ያኔ ነበር የጀመርነው።"(ገፅ፣ 74-75)

ከዚህ ከማህደረ ሰላም ንግግር የምንረዳው የስለት ልጅ መሆኗን እና ሀይማኖቷም ኦርቶዶክስ መሆኑን ይገልፅልናል።

#### 3.1.2.7 የማህደረ ሰላም ስነ ልቦናዊ አሳሳል

ማህደረ ሰላም አባቷን አብዝታ የምትወድ በምንም አይነት እንድከፋባት የማትፈልግ የእርግብ ልብ ናት። እናቷ በልጅነታቸው ምክንያቱን ባላወቀችው መንገድ ጥላቸው በመጥፋቷ እስካሁን ድረስ ምክንያቱን ባለማወቋ የምትቆጭ እና የእናቷ ድርጊት ባስታወሰችው ቁጥር አብዝታ ስትናደድ እንመለከታለን።

ማህደረ ሰላም ክፋት እና ተንኮል የሌለባት ንፁህ እና አፍቃሪ ልብ ያላት ወጣት ናት። ማህደረ አብርሃምን ከራሷ በላይ የምትወድ፣ ሙዚቃ በጣም ሰለምትወድ ከአብርሃም በመቀጠልም እቤቱ ያለውን "ሲዲ ፕሌየር" አብዝታ ትወደው ነበር። ከምግብ አይነት ደግሞ ፒዛ በጣም የምትወደው ምግብ ነው። እናቷ እና አባቷ በተለያዩ አመት ከአራተኛ ክፍል ወዴ አምስተኛ ክፍል "አልተዘዋወረችም" የሚል ካርድ ከተሰጣት በኋላ እስካሁን ድረስ በራሷ እንዳትተማመን አድርጓታል። እንደማስረጃነት በመፅፉ በራሷ አንደበት የተገለፀውን እንመልከት።

"ከዚያ በኋላ ጎበዝ ተማሪ ሆኘ ከምማርበት ክፍል፣ እስከ አጠቃላይ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ውጤት እስከ ማስመዝገብ ብደርስም ያ ቃል ያንኮታኮተው በራስ መተማመኔ ግን፣ እስከ መጨረሻው አልተመለሰም። በማንኛውም የህይወቴ ክፍል አንድም ቀን ይሰካልኛል፣ እችላለሁ የሚል እምነት ኖሮኝ አያውቅም። በየትኛውም አጋጣሚ ከውድድር እርቃለሁ።"(ገፅ፣ 106)

ከዚህ እንደምንረዳው "አልተዘዋወረችም" የሚለው ቃል ማህደረ ሰላም በእራሷ አምነት እንዳይኖራት፣ ሀቅም እያላት የተለያዩ የስራ ውድድሮችን ጨምሮ ለመሳተፍ እየፈለገች ይሄን ቃል እያስታወሰች ስትሸሽ እንደነበረ ይገልፅልናል።

ድብቅ ናት፤ ለዮናስም ከአብርሃም ጋር የነበራትን ግንኙነት አልነገረችውም። ስራዋን አብዝታ የምትወድ እና ለምትሰራበት ስራ ታማኝ ነበረች። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ወስደን እንመለከታለን።

"ለስራዋ ታማኝ ነበረች፤ ብትሞት 'ኦዲት' ያደረገችውን መስሪያቤትም ይሁን ግለሰብ ነግራኝ አታውቅም።"(ገፅ፣ 19)

ከዚህ እንደምንረዳው ማህደረ ሰላም ለአብርሃም ደበቀችው ማለት ለስራዋ በጣም ታማኝ እንደሆነች እና ስራዋን ምን ያክል እንደምትወድ ያመለክታል።

ማህደረ ሰላም ከአብረሀም ያረገዘችውን ልጅ ካስወረደች በኋላ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጉዳት ደርሶባት ነበር። ከአብርሀም ጋር ከተለያዩ በኋላ ለመርሳት ብትሞክርም አልሆን ብሏት በቀላሉ መርሳት ከብዷት ከባድ የአዕምሮ ቀውስ ውስጥ ገብታ ነበር። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ቀንጨብ አድርገን እንመለከታለን።

"የደረሰብኝ ነገር ስም የሌለው መዘበራረቅ ነው። ይኼ ነገር ወደ አእምሮ ህመም ከፍ እንዳይል ስፈራ ነው የቆየሁት። ብዙ ሴቶች በቀላሉ እንደ ቀልድ የሚያልፉት ነገር እንደሆነ አውቃለሁ፤ እኔ ግን አልቻልኩም። "(ገፅ፣ 59)

ከዚህ እንደምንረዳው ማህደረ ሰላም እና አብርሃም ከተለያየች በኋላ አብርሃምን ለመርሳት ተቸግራ ህይወቷ ሁሉ ተዘበራርቆባት እንደነበር ይገልፅልናል።

### 3.1.2.8 የማህደረ ሰላም ሞራላዊ አሳሳል

ማህደረ ሰላም በአባቷ መልካም ስነምግባር ያደገች፤ እስካሁን ድረስም ጥሩ ስነ ምግባር ያላት ሰው የምታከብር የሰውን ስሜት የምትረዳ ከእሷ ስሜት ይልቅ የሰውን ደስታ የምታስቀድም ጥሩ ባህሪ ያላት ወጣት ናት። ለአባቷ ክብር አብዝታ የምትጨነቅ ለሰው የምትራራ እና የምታዝን ሩህሩህ ልብ ያላት ናት። ማህደረ ሰላም በጣም ጨዋ ነገሮችን በመሰላትና በገመተችው መንገድ ሳይሆን የሰማችውንና ያየችውን ምንም ሳትጨምር ሳትቀንስ በዕውነት ላይ ተመርኩዛ የምትናገር አስተዋይ ናት።

### 3.1.2.9 የሃይማኖት አካላዊ አሳሳል

የሃይማኖት አካላዊ አሳሳል ስንመለከት እድሜዋ በግልፅ ባይገለፅም በ30ዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልል የምትገኝ በመልክ ያልታደለች ስትስቅ ከጥርሶቿ እና ከአይኗ በቀር ሌላው የአካል ገፅታዋ የማይስብ መልከ ጥፉ ወጣት ናት። ይህን እንደማስረጃነት በመፅሀፉ በገፅ 142 የተገለፀውን እንመለከታለን።

"መልከ ጥፉ ነኝ፣ እራሴን ጠንቅቄ አውቃለሁ። መልኬ ወንዶችን አይስብም። ከእግሮቸ እና ከጥርሴ በስተቀር ምኔም ምንም እይታ አይስብም። በእርግጥ ጓደኛዬ ማህደረ አይኖችሽ ያምራሉ ትለኛለች።"(ገፅ፣ 142)

ይህ ማለት መልከ መልካም እንዳልሆነች ወይም ወንዶችን የሚስብ ውበት እንደሌላት፣ ውበቷ አይኖቿ፣ ጥርሶቿ እና እግሮቻ ብቻ እንደሆኑ ይገልፅልናል።

መልከ ጥፉነቷ በአለባበሷ ለመሸፈን ስትል ለየት ያሉ ቀሚሶችን አዘውትራ ትለብሳለች። ይህን እንደማስረጃነት በገፅ 155 የተገለፀውን እንመለከታለን።

"የሐበሻ ቀሚስ አይነት ጥልፍ ያለው የፈረንጅ "ሚኒስከርት" ገልብጬ ታጉን ሳየው ሜድ ኢን ቻይና የሚል፣ ከቻይና ፊንላንድ፣ ከፊንላንድ ኢትዮጵያ የመጣ ከርታታ ስደተኛ ቀሚስ፤ አንች እግርሽ ያምራል፤ ሞክሪው ምናምን ብላኝ ብሩን እንኳ ገና አልከፈልኳትም እና ጓደኛዬ ቶማስ የስነ ፅሁፍ ዝግጅት አለ ብሎ ስለጋበዘኝ "ሚኒስከርቴን" ለማሳየት ነበር የሄድኩት።"(ገፅ፣ 155)

ይህ ማለት ሃይማኖት በመልክ ስላልታደለች ውበቷን ለመሸፋፈን ስትልና የወንዶችን ትኩረት ለመሳብ ወጣ ያሉ ቀሚሶችን ትለብስ እንደነበር ይገልፅልናል።

በተጨማሪም ፍላት ያለው ጫማ አዘውትራ ትጫመት ነበር። ይህን እንደማስረጃነት በገፅ 162 የተገለፀውን በመጥቀስ እንመለከታለን።

"አንዳንዶች ታዲያ እያጨበጨቡ ወደ እኔ ዞር ዞር አሉ…ግድ አልቅሽ ነው!? ወጉ አይቅር ብዬ እንዳዘነ ሰው አቀረቀርኩ። ሳቀረቅር ጫማዬን በትኩረት ተመለከትኩ፣ ለምንድን ነው ሁልጊዜ ፍላት ያለው ጫማ የማደርገው? ብዬ ያሰብኩት እና ለመጀመሪያ ጊዜ ተረከዘ ረጅም ጫማ መግዛት እንዳለብኝ የወሰንኩት በዚያች ምሽት ነበር።"(ገፅ፣ 162)

ይህ ማለት ሃይማኖት ሁልጊዜ ፍላት ያለው ጫማ ትጫመት እንዴነበርና ለምን ሁልጊዜ ፍላት ያለው ጫማ እንደምትጫመት እራሷን በመጠየቅ ከዚያ በኋላ ተረከዘ ረጅም ጫማ ለመግዛ እንዳሰበች ይገልፃል።

### 3.1.2.10 የሃይማኖት ማህበራዊ አሳሳል

የሃይማኖት ማህበራዊ አሳሳል ያላገባች፣ የተማረች፤ በትምህርቷም የመጀመሪያ ድግሪዋን በንግድ ስራ ኮሌጅ ተምራ ያጠናቀቀች ስትሆን ሁለተኛ ድግሪዋንም በምን እንደያዘች ባይገለፅም በማዕረግ ተመርቃ በታላቅ የውጭ ድርጅት በጥሩ ክፍያ ትሰራለች። ይህን እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ማህደረ ሰላም አንደበት የተገለፀውን ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ከኮሌጅ ከተመረቅን በኋላ ሃይሚን ጨምሮ ብዙዎቹ ጓደኞቼ ያውም ከእኔ ያነሰ ውጤትም፣ ብቃትም ያላቸው ልጆች በታላላቅ ድርጅቶች በጥሩ ክፍያ ሲቀጠሩ፣ ስራ ሲቀያይሩ እኔ መጀመሪያ ከተቀጠርኩበት ቢሮ ንቅንቅ አላልኩም። ስራ እንድቀይር፣ በየሚሰሩበት የውጭ ድርጅት እድሌን እንድሞክር ገፋፍተውኝ-ገፋፍተውኝ ሲደክማቸው፤ ሁሉም የራስሽ ጉዳይ ብለው ተውኝ።"(ገፅ፡ 106)

ከዚህ ከማህደረ ሰላም ንግግር የምንረዳው ሃይማኖት በማዕረግ ተመርቃ ከጨረሰች በኋላ በታላቅ ድርጅት በጥሩ ክፍያ ተቀጥራ እንደምትሰራ ይገልፅልናል።

ሀይማኖት ጥሩ ሰው ሆና ሳይሆን ክፉ ስራዋንም ሆነ ጥላቻዋን በሚስጥር ታደርገው ስለነበረ ከእናቷ በቀር ከአብሮ አደግ ጓደኛዋ ከማህደረ ሰላም፣ አብረዋት ይማሩ ከነበሩት ከክፍል ጓደኞቿ፣ በስራ ከምትገናኛቸው ጓደኞቿ እና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላት ግንኙነት ጥሩ ነበር።

ሃይማኖት ከ10ኛ ክፍል ጀምራ ኮሌጅ እስከምትገባ ወይም ጋሽ አላምነህ አሜሪካ እስከሚወጡ ድረስ በድብቅ ለ2 አመታት ያክል በእድሜ ከማይመጥናት፣ እድሜው የአባቷ ጓደኛ ሊሆን ከሚችል ሰው ጋር በፍቅር ባይሆንም ግንኙነት ነበራት። ከዚያ ወዲህም ከቶማስ ጋር የልብ ፍቅረኛሞች ባይሆኑም ለሶስት አመታት ግንኙነት ነበራት።

### 3.1.2.11 የሃይማኖት ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የሃይማኖት ስነ ልቦናዊ አሳሳል ፍቅር ፈላጊ ናት፣ ከልቡ የሚያፈቅራት ወንድ ትፈልጋለች፣ እንዲሁም በማህደረ ሰላም ቁንጅና ስለ ጥላቻዋ አንደበት አውጥታ ተናግራ ባታውቅም በልቧ ከልጅነታቸው ጀምሮ አብዝታ ትቀናባታለች። ሃይማኖት ከማህደረ በመቀጠል የምትጠላው አብርሃምን ነበር፤ የምትጠላውም ስለተነጋገሩ ወይም ስለተጋጩ ሳይሆን የማህደረ ሰላም ፍቅረኛ ስለሆነ ብቻ ነበር። ይህን እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ከዚያ ወዲህ፣ ይሄን ይሄን በተለይ ያችን ለስላሳ ቅናቴን ለማስታገስ፣ የማይገባኝን ስነ ጽሑፍ ተንተርሼ በስራው እየታከክሁ፣ ላገኘሁት ሁሉ የማይረባ ፀሐፊ መሆኑን ማወጅ ጀመርኩ።"(ገፅ፡ 157)

ከዚህ የምንረዳው ማህደረ ሰላም ለመጀመሪያ ጊዜ አብርሃምን እንዳፈቀረችሁ በነገረቻት ጊዜ ሃይማኖትም የቅናት መንፈሷን ለማስታገስ ብላ አብርሀም ጥሩ ጸሐፊ እንዳልሆነ ለአገኘችው ሰው ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻዋን እንደጀመረች ይገልፅልናን።

በራሷ አለም ወይም በምዕናቧ የሴቶቸች እኩልነት የሚል ውድድር አዘጋጅታ ማህደረ ስለ ውድድሩ ሳታውቅ ሁልጊዜ ታሸንፋት ስለነበር በሰነ ልቦናዋ ትጎዳ ስለነበር ተናደዳለች።

### 3.1.2.12 የሃይማኖት ሞራላዊ አሳሳል

ሃይማኖት በጓደኛዋ በማህደረ ሰላም ውበት ሳይቀር የምትቀና ስግብግብ ከጓደኝነት ፍቅሯ ይልቅ ጥላቻዋ የሚያመዝን በተንኮል እና በሴራ የተጠመደች ናት። የሰው ስኬት የማያስደስታት ከህፃንነቷ ጀምሮ በተለይ በማህደረ ሰላም ውድቀት የምትደስት፣ የአሸናፊነት ስሜት የሚሰማት፣ እሷን ያናቀፋት ድንጋይ ማህደረን ጥሏት ከማህደረ በላይ ደምቃ ለመታየት የምትፈልግ ክብረ ቢስ ናት። እንደማስረጃነት ከመፅሀፉ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ያቺን ድል የህፃንነት ተራ ጉዳይ አድርጌ አላያትም። ባስታወስኳት ቁጥር ነፍሴ ይደሰታል። አልተዘዋወረችም! የሚል ቃል በወርቃማ ፊደል የተፃፈ የድል ቃል ነው የሚመስለኝ።"(ገፅ: 170)

ከዚህ የምንረዳው ሃይማኖት ከህፃንነቷ ጀምሮ በማህደረ ሰላም ውድቀት ትደሰት እንደነበረ ይገልፃል።

### 3.1.2.13 የዮናስ አካላዊ አሳሳል

የዮናስ አካላዊ አሳሳሉ እድሜው በ40ዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ፣ መካከለኛ ተክለ ቁመና ያለው እና ከኋላው ፀጉሩ ላይ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ጎልማሳ ነው። ይህን እንደማስረጃነት በልቦለዱ ውስጥ አብረሃም የተናገረውን እንመለከታለን።

"ፊት ለፊት ነው የተቀመጥኩት- ከባሏ በኋላ…መልኩ አይታየኝም፤ ሁለት ጆሮዎቹ ከርፈፍ ያሉ፣ ከኋላ እንዲሁ ጎልማሳ የሚመስል፤ ፀጉሩ ላይ እንዲሁ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት።"(ገፅ፡ 47)

ከዚህ እንደምንረዳው አብረሃም ሴት ቀጥሮ ወዴ ሬስቶራንት በሚገባበት ጊዜ የበፊት ፍቅረኛው ማህደረ ሰላምን ከባሏ ጋር አግኝቷት ከርቀት ሆነው በሚተያዩበት ጊዜ ዮናስን ከኋላው ሲመለከተው ፁጉሩ ላይ ሽበት መኖሩን እና ጎልማሳ መሆኑን ይገልፅልናል።

ዮናስ በስደት የተዋወቃት ፍቅረኛው ለማስታወሻነት የሰጠችውን ብራዝሌት ከግራ እጁ ላይ አይለይም። ይህን እንደማስረጃነት ከልቦለዱ ላይ ገልፀን እንመለከታለን።

"የማህደረ ዝምታ እና ቀዝቃዛነት ሲበዛብኝ፣ ለአመታት ከእጄ ያላወለቅሁትን 'ብራዝሌት' በትካዜ እነካካለሁ።"(ገፅ: 139)

ይህ ማለት ከእጁ ላይ ብራሌት ተለይቶ የማያውቅ መሆኑን ይገልፅልናል።

### 3.1.2.14 የዮናስ ማህበራዊ አሳሳል

ዮናስ ማህበራዊ አሳሳሉ ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታውም በጣም ከፍተኛ ነው። የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ለማጠናቀቅ አንድ አመት ሲቀረው ኑሮን ለማሸነፍ ሲል በህገ ወጥ መንገድ ለ14 አመታት ያክል የወጣትነት እድሜውን በስደት አሳልፏል። ይህን እንደማስረጃነት ከልቦለዱ ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ይሁንና የበዛውን የወጣትነት ዘመኔን በስደት ተለይቻቸው ኖርኩ፤ ድፍን 14 አመታት።"(ገፅ፡ 174)

ከዚህ እንደምንረዳው ዮናስ ለእርሱ እና ለቤተሰቡ ለውጥ ሲል የወጣትነት ዘመኑን በስደት እንዳሳለፈ ይገልፅልናል።

ዮናስ ሀይማኖቱ ኦርቶዶክስ ሲሆን ቤተሰቦቹ አክራሪ ሀይማኖተኛ ስለነበሩ በወጣትነቱ ወይም ትምህርት በሚማርበት ወቅት ከሴት ልጅ ጋር እንዲገናኝ አይፈልጉም ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሴት ጋር በፍቅር የተዋወቀው በስደት ላይ ዛናታ ከምትባል ወጣት ጋር ነበር። ይህን እንደማስረጃነት ጠቅሰን እንመልከት።

"እኔ አላምንም የመጀመሪያህ ነው?" አለች እየተፍለቀለቀች! ዝም ብዬ አየኋት።

"እንዳትዋሽ" አለች ሊፈነዳ ያሰፈሰፈ ሳቋ ፊቷ ላይ እንደተዘጋጀ፤ በአዎንታ እራሴን ነቀነቅሁ፤ ከንፈሬን ስማኝ... አውቄ ነበር፤ አውቄ ነበር...እያለች በሳቅ ተፍለቀለቀች።"(ገፅ፡ 207)

ከዚህ እንደምንረዳው ዮሴፍ ሴትን ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር የተገናኘው በሰደት ላይ ከዛናታ ጋር እንደነበረ ይገልፅልናል።

ዮናስ የቤተሰቦቹ የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን አሁን ላይ ማህደረ ሰላምን አግብቶ ትዳር መስርቶ የሚኖር፣ የአንድ ሴት ልጅ አባት እና ባለቤቱ አርግዛ ሁለተኛ ልጁን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ ዮናስ ከሀይማኖት ውጭ ከቅርብ ጓደኞቹ፣ ከቤተሰቦቹ እና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታውም በጣም ከፍተኛ ነው።

## 3.1.2.15 የዮናስ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

ዮናስ ስነ ልቦናዊ አሳሳሉ ለቤተሰቦቹ ያደረገው ሁሉ የማያረካው፣ ቤተሰቦቹን አብዝቶ የሚወዳቸው፣ ያሰበውን ነገር ከማድረግ ወደኋላ የማይል መንፈሰ ጠንካራና በራስ መተማመኑ ከፍተኛ ነው። ይህን እንደማስረጃነት ጠቅሰን እንመልከት።

"አባባ በመንፈስም፣ በአካልም አዘጋጅቶኝ ነበርና ጨርሶ ይዣቸው ባልወድቅም እንደ አባባ ሆኘላቸዋለሁ ብዬ ግን አላስብም። ቢሆንም "ዋርካ በሌለበት አንቧጮ አድባር ይሆናል" እንደሚባለው የቤታችን አድባር የሆንኩት ገና በወጣትነቴ ነበር።"(ገፅ፡ 177)

ከዚህ እንደምንረዳው ዮናስ ለቤተሰቦቹ ምንም ቢያደርግ ያደረገ እንደመይመስለው፣ በመንፈሱም ጠንካራና ለቤተሰቦቹም ዋልታና መከታ እንደሆነ ያስረዳናል።

ዮናስ የሁልጊዜ ምኞቱ ልጅ እንደነበረ የቤተሰባቸውን ንብረት በሀሰት መስክረው የልብስ ሱቃቼውን የወሰዱባቸውንጨሰዎች መግደል ነበር። እንደማስረጃነት በገፅ 179 በራሱ አንደበት የተገለፀውን እንመለከታለን።

"በዚያው ሰሞን ነገሩ ተገጣጥሞ ይሁን፣ አልያም በሌላ ምክንያት ህመም የማያውቀው አባቴ ድንገት ታሞ ሆስፒታል ገባ፤ ከዚያ በኋላ ጤና አልነበረውም። የቤቱ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኔ ቀን ከሌት ህልሜ እነዚያን ከሀዲ ዘመዶቹን መግደል ነበር።"(ገፅ፡179)

ይህ ማለት የዮናስን አባት ጓደኞቹ ከድተውት ሱቁን የግላቸው አድርገውት ነበር። አባቱም ከሱቁ መዘረፍ በኋላ በንደት ስለሞት ያን ባስታወሰ ቁጥር የዘወትር ምኞቱ አባቱን የከዱትን ሰዎች መግደል ነበር።

ዮናስ ሊረሳቸው ቢሞክርም አልረሳ ያሉትን እነዚያ በስደት ላይ ያሳለፋቸውን ከባባድ የስቃይ ጊዜያቶችን እና በህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች የደረሰበትን እንግልት በባስታወሰ ቁጥር ክፉኛ ይጎዳል።

### 3.1.2.16 የዮናስ ሞራላዊ አሳሳል

ዮናስ ከሞራላዊ የገፀባህሪ የአሳሳል ደረጃ አንፃር ስናየው ስብአዊነት የሚሰማው፣ ከራሱ በላይ ለሌላ ሰው የሚያስብ የሌሎችን ህመም ለመጋራት ከተቻለም እሱ ብቻውን ለመታመም የሚሻ ጥሩ ልብ ያለው ሰው ነው። ዮናስ ቤተሰቦቹን ከራሱ አስበልጦ የሚወድ፣ ከራሱ ደስታ ይልቅ ለቤተሰቡ ደስታ የሚጨነቅ፣ አሳቢ እና ጥሩ ስነ ምግባር ያለው ሰው ነው። ይህን እንደማስረጃነት በገፅ 174 የተገለፀውን እንመለከታለን።

"በዚች ምድር፣ የመኖሬ ምክንያት የምትለው ዋናው ነገርህ ምንድን ነው? ቤተሰቤ ነው ባይ ነኝ። እንዲያው ለአፌ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ነፍሴ ውስጥ ያስቀመጠው የቤተሰብ ፍቅር፣ ለአፍታ እንኳን የማይናወጥ እንደ አለት ተራራ የፀና ነው።

"ደስታም ሆነ ሀዘኔ፣ የህይወት ውሳኔዬም ሆነ ስኬትና ውድቀቴ፣ ሁሉ በቤተሰቤ ዙሪያ ብቻ የሚያጠነጥን ነው። ያለኝን ሁሉ ነፍሴንም ቢሆን ለቤተሰቤ ሰጥቸ በምድር ላይ አለ የሚባል ደስታ ባጎናፀፋቸው ደስታዬ ነው።"(ገፅ፡ 174)

ከዚህ እንደምንረዳው ዮናስ ለቤተሰቦቹ ሲል ምንም ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል፣ ከራሱ ክብርና ደስታ በላይ ለቤተሰቡ ደስታ፣ ፍቅርና ክብር አብዝቶ የሚጨነቅ፣ ቤተሰቦቹን ከራሱ አስበልጦ የሚወድ ለራሱ ክብር የማይፈልግ ገራገር ልብ ያለው ሰው መሆኑን ይገልፅልናል።

## 3.1.3 ደካማ ጎን

የገፀ ባህሪ አካላዊ አሳሳላቸውን ተደራሲያን በቀላሉ እንዲያውቃቸው የተጠቀሱት ጥቆማዎች በቂ አይደሉም።እንደ ምሳሌ ስንገልፅ ዮናስ ገፀ ባህሪ መልኩን ጥቁር፣ ነጭ ብሎ ለማወቅ የተጠቀሱት ጥቆማዎች በቂ እንዳልሆኑና በተጨማሪም በልቦለዱ ከዚህ ባነሰ መልኩ ተስሎ በመቅረቡ ዮናስ ገፀ-ባህሪ አካላዊ አሳሳሉ እንዲህ ነው ብሎ ለመናገርም ሆነ ለመለየት አ ስ ቸ ጋ ሪ  አ ድ ር ጎ  ታ ል ። የአብርሀም ገፀ ባህሪም በተመሳሳይ ከጥቂት ጥቆማዎች ውጭ አካላዊ አሳሳሉ በደንብ ግልፅ ተደርጎ አልተሳለም። የሁለቱ ገፀ ባህሪ አካላዊ አሳሳላቸው በደንብ ባለመገለፁ ተደራሲያን አካላዊ አሳሳላቸውን በ ቀ ላ ሉ  እንዳያቁት አድርጎታል። ሌላው ዮናስ ገፀ-ባህሪ ልቦለዱ ላይ በቀሩት ሶስት የገፀ-ባህሪ አሳሳል በጥልቀት እንዳልተሳለም ተገንዝቧል። ሁለቱም ገፀ ባህሪያቶች አካላዊ አሳሳላቸው ላይ ከተገለፁት ጥቆማዎች በቀር ስለ መልካቸው እና አለባበሳቸው የተገለፀ ነገር የለም። ይህም አጥኝው የአልተዘዋወረችም ልቦለድ ደካማ ጎን መሆኑን ተረድቷል። ዮናስ ከማህበረሰቡ ጋር ያለው መስተጋብር ወይም ተግባቦት እሱም ለማህበረሰቡ ያለው አመለካከት፣ ግንኙነቱስ ምን ያክ የጠለቀ ወይም የሻከረ እንደሆን በደንብ አልገለፀውም

## 3.1.4 ጠንካራ ጎን

የአልተዘዋወረችም ረጅም ልቦለድ ጠንካራ ጎኑ ደግሞ ከጥቂት ገፀ ባህሪዎች በቀር ሌሎችን ዋና ገፀ ባህሪያት በቀላሉ በሶስቱ የገፀ ባህሪ አሳሳሎች ገልጿቸዋል። እንደምሳሌነት ስንጠቅስ የማህደረ ሰላም እና ሃይማኖት

ገፀ ባህሪዎችን ስንመለከት አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ አሳሳላቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመግለፅ ሞክሯል።

# ምዕራፍ አራት

## 4.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥንታዊ ፅሁፍ ውስጥ በዋናነት አልተዘዋወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ማለትም ከአካላዊ፣ ከማህበራዊ፣ ከስነ ልቦናዊ እና ከሞራላዊ አሳሳል አንፃር ተንትኗል። በጥናቱ ውስጥ በምእራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፤ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፤ የጥናቱን አላማ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄና ጠቀሜታ ያስቀመጠ ሲሆን እንዲሁም የጥናቱን ወሰን፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና ለችግሩ የተወሰዱ የመፍትሀ ሃሳብ አስቀምጧል። በምእራፍ ሁለት የገፀ ባህሪያት ምንነት፣ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ምንነትና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት አስቀምጧል። በምዕራፍ ሶስት የአልተዘዎወረችም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ፣ የአልተዘዎወረችም ልቦለድ ከተመረጡ ገፀ ባህሪያት ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ተንትኖ ያሉትን ጠንካራ ጎን እና ድክመቶች አስቀምጧል። አልተዘዎወረችም ልቦለድ ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ከልቦለዱ ናሙና በመውሰድ በማስረጃ ተንትኗል። አጥኝው በዚህ ልቦለድ ውሰጥ ገፀ ባህሪያት አሳሳላቸው ምን መምሰል እንዳለባቸው ትንተና አድርጓል። አልተዘዋወረችም ልቦለድ ጥሩ እና ከተወሰኑ ክፍተቶች ሌላ ሁሉንም የገፀ ባህሪት አሳሳልን አካቶ የተፃፈ ልቦለድ ነው። ነገር ግን የሚስተካከሉ አሳሳል ደረጃዎች አሉት። ልቦለዱ ማሟላት ያለባቸዉ አራቱ የገፀ ባህሪያቶች ሙሉ በሙሉ ተማልታል ማለት አይቻልም። ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንፃር ልቦለዱ በነፍስ ወከፍ መገለፅ ያለባቸውን ዋና ገፀ ባህሪያት አካላዊ መገለጫ በግልፅ ሳይሰጥ ተፅፏል። በመቀጠልም ከሞራላዊ እና ከስነ ልቦናዊ አሳሳል አንፃርም ክፍተቶች አሉበት።

## 4.2 መፍትሄ ሀሳቦች

1. የገፀ ባህሪያት አካላዊ አሳሳላቸው አንባቢያንን ሊያሻማ በማይችል መልኩ ቢገለፅ ተደራሲያን ታሪኩን እንዲወዱትና ገፀ ባህሪውን ከመረዳት አንፃር መልካም ይሆናል።

2. ዋና ገፀ ባህሪያት ግዴታ በሶስት የአሳሳል ደረጃ መሳል ስላለባቸው እና አካላዊ አሳሳል ደግሞ ከአራቱም የገፀ ባህሪያት አሳሳል ዋነኛው እና ትልቁን ድርሻ የሚወስድልን ስለሆነ ፀሀፊው የገፀ ባህሪ የአሳሳል ደረጃቸውን በጥንቃቄ ቢስላቸው ልቦለዱ በተደራሲያን ዘንድ ተወዳጅነትን ያተርፋል። ደራሲውም የራሱን ጥራት ከማሳየት አንፃር ጠቃሚና ወሳኝ ድርሻ አለውው።

3. በዚህ ልቦለድ ውስጥ ጥቂት ገፀ ባህሪያቶች ሞራላዊ አሳሳላቸው ከቤተሰቦቻቸው ውጭ ለሌላው ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከት፣ ስግብግብነታቸው ወይም የሞራል አስተማሪነታቸው በደንብ ቢገለፅ ልቦለዱ የተዋጣለት እና እንከን የማይወጣለት ይሆናል።

በአጠቃላይ ከገጸ-ባህሪያት አሳሳል አንፃር የገጸ-ባህሪያቱን አለባበስ፣ መልካቸው፣ ስለቁመናቸው፣ ስለ መጠናቸው በአግባቡ የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ ልቦለዱ ግልፅ ለማድረግ የገፀ ባህሪያቶችን አለባበስ፣ መልካቸው፣ ቁመናቸው፣ እና መጠናቸው በአግባቡ ቢገለፅ።

## ዋቢ መፅሃፍት


ያለው እንዳወቅ። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር፣ (2006)፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አ. አ።

ደበበ ሰይፉ። ከፀሐፊ ተውኔት አንፃር፣ (1973)፣ በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ አ.አ

ፋንታሁን እንግዳ። የተውኔት ኣፃፃፍ ዘዴ፣ ሶስተኛ እትም፣ (2005)፣ ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አ.አ።

ዘሪሁን አስፋው። የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን፣ (2002)፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ።

ይስማዕከ ወርቁ። የኦጋዴን ድመቶች፣ (2012)፣ ዴርቶጋዳ ማተሚያ ድርጅት፣ አድስ አበባ

ሀሪሸው። የስነ ፅሁፍ ቃላት። (1972)፣ ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ፣ ዪናይትድ ስቴት